የአማራብሔራዊክልላዊመንግሥትትምህርትቢሮ

Amhara National Regional State Education Bureau

ቁጥር ገጢ/2ዝ2/ቢ-3

ቀን 30/3/2ዐ28

ለ ሁሉ ዞኖ ብ/አስ/ዞን ትምህርት መምሪያ .

ለ ሁሉም ሪጂዮ ፖሊታን ከተማ ትምህርት መምሪያ

ባሉበት

ጉዳዩ ፡ መመሪያ ስለመላክ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በሕግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የተሸሻለውን የመምህራን ፣ የርእሰ መምህራን፣ የምክትል ርዕሰ መምህራን እና የሱፐርቫይዘሮችን የዝውውርና ምደባ አፈጻጸም መመሪያ በማሻሻልና አዳዲስ ሃሳቦችን በማካተት አውጥቷል።

በመሆኑም መመሪያው ከታህሳስ 1 ቀን/ 2018 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል እያሳሰብሁ ይኸው የጸደቀው መመሪያ በውስጡ **39** ገጽ እንደያዘ በዚሁ ደብዳቤ ሸኚነት የተላከላችሁ በመሆኑ ለተጠሪ ተቋሞቻችሁ በናንተ በኩል እንዲያውቁት እንዲደረግና ለተግባራዊነቱ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ይደረግበት ዘንድ አሳስባለሁ።

"ከሰላምታ ጋር"

ጥላሁን ወርቅነህ ተክሌ

Tilahun Workineh Teklie

ቢሮ ኃላፊ

ግልባጭ

ለምክትል ቢሮ ኃላፊ_____ ዘርፍ

ለመምህራንና ትምህርት ቤት አመራሮች ልማት ዳይሬክቶሬት

ትምህርት ቢሮ

ለአብክ መምህራን ማህበር

ባህርዳር

ለክልሉ ሲቭል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤት

ባሉበት

ስልክ/TelNo 058 220 6524/058 220 6525 ፋክስ/Fax 058 222 0814 ፖ.ሳ.ቁ 764 P.O.B

ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም

Quality Education for All

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

የተሻሻለው የመምህራን፣ ርዕሰ መምህራን፣ የምክትል ርዕሰ መምህራንና የሱፐርቫይዘሮች የዝውውርና ምደባ አፈፃፀም መመሪያ

መመሪያ ቁጥር.19/2018

ህዳር 2018 ዓ.ም
ባህርዳር

መመሪያ ቁጥር 19/2018ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

የተሻሻለው የመምህራን፣ ርዕሰ መምህራን፣ የምክትል ርዕሰ መምህራንና የሱፐርቫይዘሮች

የዝውውርና ምደባ አፈፃፀም መመሪያ

በክልሉ በተፈጠረው የፀጥታ ችግር ምክንያት አንዳንድ ሠላምና መደበኛ ሥራ ወደ አለበት ቦታ በአስተዳደራዊ ውሣኔ በጊዜያዊ ዝውውር የተመደቡ መርሱና መደበኛ ዓመታዊ ዝውውሩ ለሁለት አመታት ሣይሠራ በመቆየቱ የዝውውር ዕድል አጥተው የቆዩ መርሱን ችግር ሊፈታ የሚችል የዝውውር ሥርዓትን በሕግ አሻሽሎ ገቢራዊ ማድረግ በማስፈለጉ፤

ከአቅም በላይ በሆኑ የፀጥታ ችግሮች ምክንያት በነባሩ የዝውውር መመሪያ ሊፈፀሙ የማይችሉ ድንጋጌዎችን በመለየት መመሪያውን ከወቅቱ ጋር ተጣጥሞ እንዲፈፀም ማድረግ የሚያስችል አድርጎ እንደገና መቅረጽ በማስፈለጉ፤

የዝውውር ሥርዓቱን ቀልጣፋ በማድረግ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች በተመደቡበት ቦታ ተረጋግተው እንዲሠሩ ለማድረግ ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑ ስለታመነበት፤

ፍትሐዊና ግልጽ የሆነ የሥራ ቦታ ዝውውር በማከናወን የመምህራንንና የትምህርት ቤት አመራሮችን እርካታ ለማሳደግ ፋይዳው የጎላ መሆኑ ስለታመነበት፤

አሳታፊ እና ተጠያቂነት ያለበት ዝውውር በማከናወን በዘርፉ የሚታየውን የሰው ኃይል ስምሪት ምጥጥንን በማረጋገጥና የተማሪዎችን ውጤታማነት ከፍ ለማድረግ አሥፈላጊ በመሆኑ፤

ታታሪና ብቃት ያላቸውን መምህራን፣ ርዕሰ-መምህራን፣ ምክትል ርዕሰ-መምህራንና ሱፐርቫይዘሮችን ወደ ሙያው ለመሳብና በሙያው እንዲቆዩ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የክልሉ ትምህርት ቢሮ የአማራ ክልል አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር.300/2017 አንቀጽ-34 ንዑስ አንቀጽ-28 እና አንቀጽ-19 ንዑስ አንቀጽ-1 ፊደል ተራ (ሰ) ላይ በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አሻሽሎ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የተሻሻለው የመምህራን፣ የርዕሰ-መምህራን፣ የምክትል ርዕሰ-መምህራንና የሱፐርቫይዘሮች የዝውውርና ምደባ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር.19/2018 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ "ቢሮ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ ነው፤

2/ "መምህር" ማለት ከመንግሥት መምህራን ትምህርት ኮሌጆች ወይም ከመንግሥት ዩኒቨርስቲዎች ወይም የመምህርነት ሥልጠና እንዲሰጡ በሕግ ተፈቅዶላቸው ከነበሩ የግል ኮሌጆች ወይም ዩኒቨርሲቲዎች በመደበኛው ወይም በማታው ወይም በክረምት ወይም በርቀት መርሃ ግብር በማስተማር ሙያ ሥልጠና በመከታተል በምስክር ወረቀት /ሰርተፊኬት/ወይም በዲፕሎማ ወይም በመጀመሪያ ዲግሪ ወይም በሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ ተመርቆ በመሥራት ላይ ያለ ሆኖ ዝውውር ወይም ምደባ የሚፈጸምለት ሰው ነው፤

3/ "ትምህርት ቤት" ማለት በክልሉ ውስጥ ተቋቁሞ በመንግሥት ይዞታ ስር የሚተዳደር ከቅድመ- አንደኛ ደረጃ እስከ 2ኛ ደረጃ ያለ የትምህርት ተቋም ነው፤

4/ "ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት" ማለት በክልሉ ውስጥ ተቋቁሞ በመንግሥት ይዞታ ስር የሚተዳደር ራሱን የቻለ ግቢ ያለው ወይም በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክልል ውስጥ ራሱን የቻለ መማሪያ ክፍሎች ያሉት ተቋም ነው፤

5/ "የትምህርት ቤቶች ጉድኝት" ማለት አንድን ትምህርት ቤት ማዕከል በማድረግ በመልክዓ-ምድር የተቀራረቡ ትምህርት ቤቶች በጋራ የትምህርት ሥራ ለመሥራት እንዲችሉ የተፈጠረ አደረጃጀት ነው፤

6/ "ርዕሰ-መምህር" ማለት አንድን ትምህርት ቤት በኃላፊነት የሚመራ የትምህርት ቤት የበላይ አመራር ነው፤

7/ "ምክትል ርዕሰ-መምህር" ማለት አንድን ትምህርት ቤት በምክትል ኃላፊነት የሚመራ የትምህርት ቤት አመራር ነው፤

8/ "ሱፐርቫይዘር" ማለት የተጎዳኙ ትምህርት ቤቶችን በኃላፊነት የሚመራ የሚደግፍና የሚያስተባብር አመራር ነው፤

9/ "የትምህርት ባለሙያ" ማለት በየደረጃው በሚገኝ የትምህርት መዋቅር በዓላማ ፈጻሚነት ተመድቦ በመስራት ላይ የሚገኝ ነው፤

10/ "መርሱ" ማለት መምህራን፣ ርዕሰ-መምህራን፣ ምክትል ርዕሰ-መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ነው፤

11/ "አገልግሎት" ማለት ሕጋዊ እውቅና ካላቸው የግል፣ የመንግሥት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ በመቀጠር በየወሩ የሥራ ግብር የሚከፈልበት ቋሚ ደመወዝ እየተከፈለው ሥራውን ለሚያሠራው መሥሪያ ቤት በመደበኛ የሥራ ሰዓት የተወሰነ ሥራ በማከናወን የተገኘ የሥራ ልምድ ነው፤

12/ "አግባብ ያለው አገልግሎት" ማለት በመምህርነት፣ በትምህርት ቤት አመራርነት፣ በዓላማ ፈጻሚ የትምህርት ባለሙያነት ወይም በትምህርት አመራርነት የተቀሰመ የሥራ ልምድ ነው፤

13/ "ዝውውር" ማለት መምህራን፣ ርዕሰ-መምህራን፣ ምክትል ርዕሰ-መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ከሚሠሩበት ትምህርት ቤት፤ ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም ክፍለ-ከተማ፤ ዞን ወይም ሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ ወይም ብሔረሰብ አስተዳደር ትምህርት መምሪያ፤ ክልል ትምህርት ቢሮ ወደ ሌላ ትምህርት ቤት፤ ወረዳ ወይም ከተማ አሥተዳደር ወይም ክፍለ-ከተማ፤ ዞን ወይም ሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ ወይም ብሔረ-ሰብ አስተዳደር ትምህርት መምሪያ፤ ክልል ትምህርት ቢሮ በየትምህርት ዘመኑ መጨረሻ አንድ ጊዜ በአገልግሎትና ሌሎች የዝውውር መስፈርቶች ከአቻዎቻቸው ጋር ተወዳድረው ለዝውውር በቀረበ ፍላጎት ወይም በወጣ-ገባ በሚገኝ ክፍት የሥራ ቦታ ለመሥራት የሚደረግ የሥራ ቦታ ለውጥ ነው፤

14/ "የትምህርት ቤት አመራር" ማለት የመንግሥት ቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ አንደኛ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን በመምራት ላይ ያለ ርዕሰ-መምህር፣ ምክትል ርዕሰ-መምህር ወይም ሱፐርቫይዘር ነው፤

15/ "ለኑሮ አስቸጋሪ ቦታ" ማለት በአየር ጠባይ ተስማሚ አለመሆንና በመሠረተ ልማት አለመሟላት የተለየ ቦታ ነው፤

16/ "ተመራጭ" ማለት ከቀበሌ እስከ ክልል ደረጃ ባሉ የሕዝብ ምክር ቤቶች በሕዝባዊ ምርጫ ወይም ከወረዳ እስከ ክልል ባለ መዋቅር በመምህራን ማሕበር አመራርነት ተመርጦ የሚሠራ ነው፤

17/ "ተጠሚ" ማለት በክልሉ ምክር ቤትና በየደረጃው በሚገኙ ምክር ቤቶች፣ እንዲሁም በርዕሰ-መስተዳድር ውክልና በተሰጠው አካል ወይም በብሔረ-ሰብ ዞን አስተዳዳሪዎች

ወይም በብሔረ-ሰብ ወረዳ አስተዳዳሪዎች ወይም በወረዳ አስተዳዳሪዎች ወይም በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ጉባኤ የመንግሥት ተቋማትን እንዲመራ በሹመት የሚመደብ ኃላፊ ነው፤

18/ **"ትምህርት ደረጃን ማሻሻል"** ማለት በዲፕሎማ፣ በመጀመሪያ ዲግሪ፣ በሁለተኛ ዲግሪ በመንግሥት በጀት ወይም በግል በመማር የትምህርት ደረጃ ለውጥ ማድረግ ነው፤

19/ **"የጋብቻ ማስረጃ"** ማለት ሕጋዊነት ባላቸው ተቋማት ማለትም በማዘጋጃ ወይም በክብር መዝገብ ሹም ፊት፣ በባህላዊ ወይም በሃይማኖታዊ የጋብቻ አፈጻጸም ሥርዓት ወይም በወላጃ ኩነት ምዝገባ የተፈጸመ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ነው፤

20/ **"የህክምና ማስረጃ"** ማለት የህክምና አገልግሎቱ ከተሰጠበት የጤና ድርጅት በሦስት ሀኪሞች/የሃኪሞች ቦርድ/ የሚሰጥ የመርሱን የጤና ሁኔታ የሚገልጽ የምስክር ወረቀት ነው፤

21/ **"አካል ጉዳተኛ"** ማለት በደረሰበት የአካል፣ የአዕምሮ ወይም የስሜት ህዋሳት ጉዳት ተከትሎ በሚመጣ የማኅበራዊ ፤የኢኮኖሚ መድሎ ወይም ባህላዊ መድሎ ሳቢያ በስራ ስምሪት፤ ዝውውር እና ምደባ ስራ ላይ እኩል ተጠቃሚ ያልሆነ ሰው ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሙሉ በሙሉ ማንበብና መጻፍ በማያስችል ሁኔታ አይነ-ስውር የሆነ ወይም ሙሉ በሙሉ መስማት የተሳነው፣ ወይም በተጨማሪ የአካል ድጋፍ የሚንቀሳቀስ ወይም በግልጽ በሚታይ ሁኔታ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት በአጋጠመው ጉዳት የተነሳ በመምህራን ልማት የሚፈረጅ ከባድ የእንቅስቃሴ ችግር ያለበት ሰው ማለት ነው፤

22/ **ቋሚ የሥራ ቦታ ምደባ"** ማለት አዲስ ምደባ የተሠጣቸው ወይም ቅጥር የተፈጸመላቸው መምህራንን በመደበኛ ዝውውር ወቅት አገልግሎታቸውን መሠረት በማድረግ ክፍት በሆኑ ዞኖች፣ ብሔረ-ሰብ አስተዳደር ወይም ሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ ትምህርት መምሪያዎች፣ ወረዳዎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች ወይም ክፍለ-ከተማ ወይም ትምህርት ቤቶች መመደብ ሲሆን የትምህርት ደረጃቸውን ያሻሻሉ መምህራንንና ጊዚያዊ ምደባ የተሠጣቸውን የትምህርት ቤት አመራሮች በወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም በክፍለ-ከተማ ውስጥ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች አገልግሎታቸውን መሠረት በማድረግ መመደብ ነው፤

23/ **"ጊዚያዊ የስራ ቦታ ምደባ"** ማለት የትምህርት ዘመኑ መደበኛ ዝውውር ከተፈጸመ በኋላ በአዲስ የሚቀጠሩ ወይም በማህበራዊ ችግር ምክንያት በጊዚያዊነት የሚመደቡ ወይም የትምህርት ደረጃቸውን አሻሽለው የትምህርት ደረጃው የተያዘላቸውን ወይም የሰው ኀይል ክምችት ካለበት ትምህርት ቤት ወይም ወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤት ወይም

ክፍለ -ከተማ ወይም ሪጂዮ -ፖሊታን ከተማ ትምህርት መምሪያ ወደ ሌላ ቦታ እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ በጊዚያዊነት መምህራንን መመደብ ነው፤

24/ **"ወጣ-ገባ ዝውውር"** ማለት መደበኛ ዝውውር በሚሠራበት ጊዜ መርሱ ዝውውር በማግኘታቸው በሚለቀቁ ክፍት የሥራ ቦታዎች ሌሎች መስፈርት የሚያሟሉ መርሱን መተካት ነው፤

25/ **"የትምህርት ደረጃ"** ማለት የመምህርነት ሥልጠና እንዲሰጡ እውቅና ከተሰጣቸው የመንግስት መምህራን ትምህርት ኮሌጆች ወይም የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች በቀን፣ በማታ ወይም በርቀት ወይም በክረምት መርሀ ግብር የሚሰጠውን ትምህርት በመማር የተገኘ ሠርተፊኬት ወይም ዲፕሎማ ወይም የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም 2ኛ ዲግሪ ነው፤

26/ **"የትምህርት ዝግጅት"** ማለት የመምህርነት ስልጠና እንዲሰጡ እውቅና ከተሰጣቸው የመንግስት መምህራን ትምህርት ኮሌጆች ወይም የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች በቀን ወይም በማታ ወይም በርቀት ወይም በክረምት ፕሮግራሞች የሚሰጠውን ትምህርት በመከታተል የተገኘን የትምህርት አይነት የሚገልጽ ነው፤

27/ **"ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ/ተሙማ"** መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች በማስተማር ወይም በትምህርት ቤት አመራርነት ሥራ ላይ እስካሉ ድረስ ፍላጎትን መሰረት ባደረገና ከሚያስተምሩት ትምህርት ይዘት ወይም የማስተማር ሥነ-ዘዴን መሠረት ያደረገ ትምህርት ቤት ተኮር ሥልጠና ነው፤

28/ **"የዝውውር ኮሚቴ"** ማለት በየደረጃው ከሚገኙ የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ባለሙያዎችና የመምህራን ማሕበር ተመራጮች በሚወከሉ አካላት ለዝውውር ተግባር የሚቋቋም አካል ነው፤

29/ **"ሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ"** ማለት የአንድን ከተማ ሁለንተናዊ ልማት ከማፋጠን አንፃር ዓይነተኛ ማዕከል በመሆን በዙሪያው የሚገኙትን አነስተኛ ከተሞች ይዞ ወይም አጠቃሎ እንዲያድግ ለተመረጠ ለማናቸውም የክልሉ ከተማ የተሰጠ መጠሪያ ነው፡፡

30/ **"ክፍለ-ከተማ"** ማለት በሪጂዮ-ፖሊታንና እንደ ከተማው የዕድገት ሁኔታ በፈርጅ አንድ ስር በሚጠቃለሉ ከተሞች ቀጥሎ የሚገኝ የአስተዳደር እርከን ነው፤

31/ **"ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት"** ማለት በፍትሐብሄር ሕጉ አንቀፅ-1793 ላይ የተገለፀው ትርጉም ማለትም በመርሱ ላይ የደረሰ ያልታሰበ ድንገት ደራሽ ነገሮች፤ በመንግስት የሚደረግ ክልከላ፤ እንደ መሬት መናወፅ፤ መብረቅ፤ ማዕበል፤ መሠል ፍጥረታዊ መቅሠፍት፤ የጠላት የውጭ አገር ጦርነትና የአገር ውስጥ ጦርነት፤ ሞት፤ ባልታሰበ

ሁኔታ የሚደርስ ከባድ አደጋ ወይም ፅኑ ህመምን የሚመለከት ሆኖ በተለይም የመርሱ ዝውውርና ምደባ ሂደት እንዳይከናወን የሚያደርግ የፀጥታ ችግርን የሚያካትት ነው፤

32/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

33/ በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴት ፆታንም ይጨምራል፤

3. የተፈጻሚነት ወሰን፤

ይህ መመሪያ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ውስጥ በሚገኙ የመንግሥት የቅድመ-አንደኛ ደረጃ፣ የአንደኛ ደረጃ፣ የመካከለኛ ደረጃ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና የተጎዳኙ ትምህርት ቤቶች ማዕከላት እና መርሱዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

ዝውውሩ የሚፈጸምባቸው ደረጃዎችና የሚመለከታቸው ጉዳዮች

4. ዝውውሩ የሚፈጸምባቸው ደረጃዎች፤

1/ በቢሮ ደረጃ የሚሠራ ዝውውር፤-

የክልል ትምህርት ቢሮዎች፣የዞን ትምህርት መምሪያዎች ፣የብሔረ-ሰብ አስተዳደር ትምህርት መምሪያዎች፣ የሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ ትምህርት መምሪያዎች እንዲሁም የወረዳ እና ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤቶችን በሚቀርብ አዲስ ፍላጎት ፣ በወጣ-ገባ እንዲሁም በሪጅዮ ፖሊታን ከተሞች ጊዜያዊ የስራ ቦታ ምደባ የተሠጣቸውን መርሱ ሆኖ ለመዛወር የሞሉትን የመደበኛ ዝውውር ቦታ እና በወጣ-ገባ የሚገኘውን ክፍት ቦታ መነሻ በማድረግ በመጀመሪያ ደረጃ የሚሰራ ዝውውር ይሆናል፡፡

2/ በዞን፣ በብሔረሰብ አሥተዳደር፣ በሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ ትምህርት መምሪያ ደረጃ የሚሠራ ዝውውር፤-

ከክልል ትምህርት ቢሮ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ምደባ ሣይሠጣቸው በዝውውር የተላከለትን መርሱ በመቀበልና በወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት፣ በከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት እንዲሁም በክፍለ-ከተማ ደረጃ ለመዛወር የሞሉትን መርሱ አካቶ በአዲስ በሚቀርብ ፍላጎትና በወጣ-ገባ በሚለቀቅ ክፍት የሥራ ቦታ ከአቻዎቻቸው ጋር በማወዳደር በሁለተኛ ደረጃ የሚሠራ ዝውውር ይሆናል፡፡

3/ በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደርና በክፍለ ከተማ ደረጃ የሚሠራ ዝውውር፤-

ከዞን ትምህርት መምሪያ፣ ከብሔረሰብ አሥተዳደር ትምህርት መምሪያ፣ ከሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ ትምህርት መምሪያ በዝውውር የተላከለትን መርሱ በመቀበል የትምህርት ቤት እና የጉድኝት ደረጃ ዝውውር የሞሉትን አካቶ በሚቀርብ ፍላጎትና በወጣ-ገባ በሚለቀቅ

ክፍት የሥራ ቦታ ከአቻዎቻቸው ጋር በማወዳደር በሦስተኛ ደረጃ የሚሠራ ዝውውር ይሆናል፡፡

5. **የዝውውርና ምደባ ሥራ ከመፈጸሙ በፊት በትኩረት መከናወን ያለባቸው ተግባራት፤**

1/ መርሱ ከሚሠሩበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመዛወር በቅድሚያ በትምህርት ቤት ደረጃ በሚተገበረው የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ ሥልጠና እየተሳተፉ መሆኑን በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህርና በጉድኝት ሱፐርቫይዘሩ መረጋገጥ አለበት፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ-1 የተመለከተው ቢኖርም፣ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት ትምህርት ቤቱ ሥራ በማቋረጡ ወይም ሥራ ባለመጀመሩ ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና ያልወሰዱ መርሱ በማንኛውም የዝውውር ደረጃ አመልክተውና ተወዳድረው ከመዛወር አይከለከሉም፤

3/ መርሱ ከሚሠሩበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመዛወር በቅድሚያ የዝውውር ቅጹ ላይ በትክክል መሙላት አለባቸው፤

4/ በትምህርት ደረጃ እና ዝግጅት ተጨማሪ የሰው ኀይል ማስፈለጉንና በትምህርት ቤቶች በትርፍነት የሚመደቡ መምህራን አለመኖራቸው አስቀድሞ መረጋገጥ አለበት፤

5/ የዝውውር መጠየቂያ ፎርም ዝውውሩ ለሚመለከታቸው መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ እንዲደርስ መደረግ አለበት፤

6/ መምህራን፣ ርዕሰ-መምህራንና ምክትል ርዕሰ-መምህራን በትምህርት ቤት ደረጃ እንዲሁም ሱፐርቫይዘሮች በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ወይም በክፍለ-ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤቶች ደረጃ ዝውውር ስለመሙላታቸው በፊርማቸው የተረጋገጠ መሆኑን፤ በፊርማቸው ያላረጋገጡ ከሆነ ዝውውር እንዳልሞሉ ተቆጥሮ ከውድድር ውጭ የሚደረጉ ይሆናል፤

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 እና 6 የተመለከቱት ቢኖሩም፣ ከመርሱዎች አቅም በላይ በሆነ የጸጥታ ችግር ምክንያት በትምህርት ቤት ደረጃ ቀርበው በፊርማቸው የተረጋገጠ የዝውውር ፎርም ሞልተው መወዳደር ያልቻሉ መርሱዎች የፀጥታ ችግር በሌለባቸውና አመች በሆነላቸው የሪጅዮ ፖሊታን ከተማ ትምህርት መምሪያዎች ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የወረዳ ትምህርት ፅሕፈት ቤቶች ድረስ በመቅረብ ዝውውር ፎርም ሞልተው መወዳደር የሚችሉ ይሆናል፤

8/ ዝውውሩን በአግባቡ ለመፈጸም መምህራን፣ ርዕሰ-መምህራን፣ ምክትል-ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የዝውውር ፍላጎት ማሳወቂያ ቅጽ በጥንቃቄ በወቅቱ ተሞልቶ በየደረጃው

ለሚገኙ የትምህርት ቢሮ የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራር ቡድን ወይም ዳይሬክቶሬት መድረስ አለበት፤

9/ ከሁለቱ አንዱ ተጋቢ የመንግሥት ተቀጣሪ ሠራተኛ ሆኖ መርሱ ለጋብቻ በተሠጠው ኮታ ለመወዳደር ካመለከተ የጋብቻ ማስረጃው ዝውውር ከመሞላቱ አንድ ዓመት ቀደም ብሎ ከሁለቱም ተጋቢዎች ማህደር ውስጥ የታሰረ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅበታል፤

10/ ዝውውር በሚሰራበት ወቅት ከጥንዶች አንዱ በዕድሜ ምክንያት በጡረታ የተሰናበቱ ወይም በሞት የተለዩ ከሆነ ጡረታ ከመውጣቱ ወይም በሞት ከመለየቱ በፊት የነበረ አገልግሎት ለዝውውር የሚያዝ አይሆንም፤

11/ አንድ ዝውውር የሚሞላ መምህር፣ ርዕሰ-መምህር፣ ምክትል ርዕሰ-መምህር ወይም ሱፐርቫይዘር ለክልል፣ ለዞን፤ ለብሔረ-ሰብ አስተዳደር፣ ለሪጂየ-ፖሊታን ከተማ፣ ለወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት፣ ለከተማ አስተዳደር ወይም ለክፍለ-ከተማ ሁለት አማራጮችን መሙላት ይችላል፤ ዝውውሩም እንደ ምርጫው ቅደም ተከተል የሚታይ ሆኖ ከተጠቀሰው አማራጭ ኮድ ብዛት ውጭ ተጨማሪ ኮድ ተሞልቶ ከተገኘ የተሞላው ዝውውር የሚሰረዝ ይሆናል፤

12/ አንድ መምህር፣ ርዕሰ-መምህር፣ ምክትል ርዕሰ-መምህር ወይም ሱፐርቫይዘር ለጉድኝት ማዕከላት ወይም ለትምህርት ቤት ሦስት አማራጮችን ማቅረብ ይችላል፤ ዝውውሩም እንደ ምርጫው ቅደም ተከተል የሚፈጸም ሆኖ ከተጠቀሰው አማራጭ ኮድ ብዛት ውጭ ተጨማሪ ኮድ ተሞልቶ ከተገኘ የተሞላው ተጨማሪ ኮድ የሚሰረዝ ይሆናል፤

13/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 11 እና 12 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልል ደረጃ ለሚሰራ የዞን ዞን ዝውውር በሶስተኛ ምርጫነት በዞን ወይም በብሔረ-ሰብ አስተዳደር ውስጥ ባለ በየትኛውም ወረዳ ለመዛወር ፈቃደኛ ከሆነ በዞኑ ወይም በብሔረ-ሰብ አስተዳደሩ ውስጥ ለማንኛውም ወረዳ የተቀመጠውን ኮድ በሶስተኛ ምርጫነት መሙላት ይችላል፤

14/ መርሱ በፀጥታ ችግር ምክንያት አመች በሆነላቸው የዞን ወይም የሪጅዮ ፖሊታን ከተማ ትምህርት መምሪያዎች ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የወረዳ ትምህርት ፅሕፈት ቤቶች በኩል ቀርበው የሞሉት ዝውውር ስህተት የሌለበት ስለመሆኑ በሞሉበት የትምህርት መዋቅር የውስጥ ማስታወቂያ ሰሌዳ ቢያንስ ለአምስት የስራ ቀናት በግልፅ ተለጥፎ እንዲያውቁት መደረግ አለበት፡፡

15/ መርሱ ፈርመው የሞሉት የዝውውር መመ.ያ ፎርም ከመላኩ በፊት የተሞላው የቦታ ኮድ በዞኑ ወይም በብሔረ-ሰብ አስተዳደሩ ውስጥ ለሚገኙ ወረዳዎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች የተሰጠ ኮድ ስለመሆኑ ዝውውሩን ያስሞላው የትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ሴክተር ኃላፊ ማረጋገጥ አለበት፤

16/ በመደበኛ ዝውውር ወቅት ከሌላ ቦታ የመጡ መምህራን፣ ርዕሰ መምህራን፣ ምክትል ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ያለምንም ልዩነት እኩል በወረዳው ወይም ከተማ አስተዳደሩ ወይም ክፍለ-ከተማው ካሉ መምህራን ጋር በአገልግሎታቸው ተወዳድረው በሚመጥናቸው ቦታ በቋሚነት የሚመደቡ ይሆናል፤

17/ በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ወይም በክፍለ-ከተማ ደረጃ የተጠናቀረውን የመርሱ ዝውውር መረጃ በፀጥታ ችግር ምክንያት በጉድኝት ማዕከላት ወይም በወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤት መለጠፍ ባልተቻለ ጊዜ እንዳግባብነቱ ለዞን ወይም ክልል ከመላኩ በፊት መርሱ ሊመለከቱት በሚችል አመች የወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤት ወይም ዞን ትምህርት መምሪያ የውስጥ ማስታወቂያ ለ5-ተከታታይ ቀናት ተለጥፎ እንዲያውቁት መደረግ አለበት፡፡

18/ አዲሱ ስርዓተ ትምህርት ተግባራዊ መሆኑን ተከትሎ የቴክኒካል ድሮዊንግ ትምህርትን ሲያስተምሩ የነበሩ መምህራን ሲሠጥ የነበረው ትምህርት በመታጠፉ በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሂሳብ ወይም ፊዚክስ ወይም ኬሚስትሪ እንዲያስተምሩ እንዲሁም በመካከለኛ ደረጃ ሂሳብ ወይም አጠቃላይ ሳይንስ እንዲያስተምሩ የተመደቡ መምህራን የዝውውር ፎርም የሚሞሉት ተመድበው እያስተማሩ ባሉበት የትምህርት ዝግጅት እና የትምህርት እርከን ብቻ ይሆናል፤

19/ አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ተግባራዊ መሆኑን ተከትሎ የጄኔራል ቢዝነስ ትምህርትን ሲያስተምሩ የነበሩ የሚሰጠው ትምህርት በመታጠፉ በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኢኮኖሚክስን እንዲያስተምሩ የተመደቡ መምህራን የዝውውር ፎርም የሚሞሉት ተመድበው እያስተማሩ ባሉበት የትምህርት ዝግጅት ብቻ ይሆናል፤

20/ በባዮሎጂ ወይም በጂኦግራፊ የትምህርት ዝግጅት ተመርቀው በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እርሻ የቀለም ትምህርትን የሚያስተምሩ መምህራን በእርሻ ትምህርት አስተማሪነት ብቻ የዝውውር ፎርም እንዲሞሉ ይደረጋል፤

21/ ዞኖች ወይም ብሔረ-ሰብ አስተዳደሮች ወይም ሪጂዮ-ፖሊታን ከተማዎች ያጠናቀሩትን የዝውውር መረጃ ወደ ክልል ከመላካቸው በፊት መረጃው ትክክል ስለመሆኑ በዝውውር ኮሚቴ መረጋገጥ ይኖርበታል።

ክፍል ሶስት

የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች የዝውውር አፈጻጸም

የነጥብ አሠጣጥና የዝውውር ሂደት

6. **የነጥብ አሰጣጥ፤**

1/ በትምህርት ደረጃ እና በትምህርት ዝግጅት ከቀረበው ፍላጎት እና በዝውውር ወቅት በወጣ ገባ በሚለቀቁ ክፍት ቦታዎች 70% አገልግሎትን መሠረት አድርጎ ይታያል፤

2/ በትምህርት ደረጃ ከቀረበው ፍላጎት እና በወጣ ገባ 15% ለተጎጂዎች ወይም ለተመራጮች የትዳር አጋሮቻቸው ዝውውር የሚታይ ይሆናል፤

3/ በትምህርት ደረጃ በቀረበው ፍላጎት እና ወጣ ገባ 15% ለጋብቻ የሚሰጥ ሲሆን ለትዳር የሚሰጠው 15% ተግባራዊ የሚደረገው በመንግሥት ሥራ ምክንያት የተራራቁ ባለትዳሮችን ለማቀራረብ ብቻ ይሆናል፤

4/ ለጋብቻና ለሹመት የተሰጠውን ኮታ መጠቀም የሚቻለው መርሱ ካለበት የሥራ ቦታ የትዳር አጋሩ ወደ አለበት ሌላ የሥራ ቦታ ለመዛወር ወይም ለመቅረብ ከሆነ ዝውውር የሞላው መርሱ በስሌት ተባዝቶ ባገኘው የራሱ አገልግሎት ብቻ ይሆናል፤

5/ በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ደረጃ የትምርት ቤት ትምህርት ቤት ዝውውር በሚሠራበት ወቅት የአካል ጉዳተኞችን የትምህርት ደረጃና የሠለጠኑበትን የትምህርት ዝግጅት መሠረት በማድረግ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ-1 ለአገልግሎት ከተሰጠው 70% ኮታ ውስጥ በ20% የሆነውን ኮታ ብቻቸውን እርስ በእርሣቸው ከሁሉም በቀዳሚነት እንዲወዳደሩበት ይደረጋል፤

6/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ-1 እና 5 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልል ደረጃ በሚሰራው የዞን ዞን ዝውውር በስሌት ተባዝቶ አካል ጉዳተኞች ካላቸው ድምር አገልግሎት ላይ ለወንድ አካል ጉዳተኛ ሦስት ዓመት አገልግሎት ፤ ለሴት አካል ጉዳተኛ አራት ዓመት አገልግሎት፤ በዞን ደረጃ በሚሰራው የወረዳ ወረዳ ዝውውር ለወንድ አካል ጉዳተኛ ሁለት አገልግሎት፤ ለሴት አካል ጉዳተኛ ሦስት ዓመት አገልግሎት ለዝውውር ውድድሩ ተጨምሯቸው የሚወዳደሩ ይሆናል።

7. **የዝውውር አፈጻጸም ሂደት፤**

1/ ዝውውር የሚፈጸመው ከሚፈለገው የሰው ኀይል ብዛት አንጻር ለመምህራን የትምህርት ደረጃንና የትምህርት ዝግጅትን መሠረት በማድረግ ሲሆን ለርዕሰ-መምህራን፣ ለምክትል ርዕሰ-መምህራንና ለሱፐርቫይዘሮች የትምህርት ደረጃንና የአመራርነት ዓይነትን መሠረት በማድረግ ይሆናል፤

2/ የትምህርት ቤት አመራሮች ዝውውር በሚሰራበት ወቅት ቅድሚያ ተፈላጊ የትምህርት ደረጃን ያሟሉት በአመራርነት አይነት እርስ በእርሳቸው የሚወዳደሩ ሲሆን በመቀጠል ትምህርት ቤቶችን ወይም ጉድኝት ማዕከላትን በተጠባባቂነት እየመሩ ያሉ አመራሮች በወረዳው ወይም በከተማ አስተዳደሩ ወይም በክፍለ ከተማው ሥር ለሚገኙ ትምህርት ቤቶች ወይም ጉድኝት ማዕከላት እርስ በእርሳቸው እንዲወዳደሩ ይደረጋል፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፤-

ሀ) በየደረጃው በሚሰራው ዝውውር በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማስተማር ላይ ያሉ የመጀመሪያ እና የ2ኛ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ ያላቸው መምህራን በሚቀርበው ፍላጎት እና በወጣ ገባ በሚለቀቅ ቦታ 50% በ2ኛ ዲግሪ የሚሞላ ሲሆን 50% በመጀመሪያ ዲግሪ የሚሞላ ይሆናል፤ ሆኖም በሚቀርበው ፍላጎት እና በወጣ ገባ በሚለቀቅ ቦታ የሚሰራው ዝውውር ለሁለቱም የትምህርት ደረጃዎች እኩል የማይደርስ ከሆነ ቅድሚያ የሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ ላለው ይሠጣል፡፡

ለ) በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማስተማር ላይ ያሉ የዲፕሎማ እና የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ ያላቸው መምህራን በሚቀርበው ፍላጎት እና በወጣ ገባ በሚለቀቅ ቦታ 50% በመጀመሪያ ዲግሪ የሚሞላ ሲሆን 50% ዲፕሎማ የሚሞላ ይሆናል፡፡ ሆኖም በሚቀርበው ፍላጎት እና በወጣ ገባ በሚለቀቅ ቦታ የሚሰራው ዝውውር ለሁለቱም የትምህርት ደረጃዎች እኩል የማይደርስ ከሆነ ቅድሚያ የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ ላለው ይሠጣል፤

ሐ) በዲፕሎማ የትምህርት ደረጃ ተመርቀው ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል እንዲያስተምሩ የተፈቀደላቸውና ከ1ኛ-6ኛ ክፍል ዝውውር የሞሉ መምህራን መዛወር የሚችሉት ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል በቀረበው ፍላጎት እና በወጣ ገባ በተለቀቀ ክፍት ቦታ ይሆናል፡፡

መ) በተለያዩ የትምህርት ዝግጅቶች ተመርቀው በክፍል ምደባ መመሪያ መሠረት በማስተማር ላይ የሚገኙ መምህራን በሚቀርበው ፍላጎት ወይም በወጣ ገባ በሚከፈት ቦታ በመመሪያው እንዲያስተምሩ በተፈቀደው የትምህርት ዝግጅት የመዛወር መብት አላቸው፡፡

4/ የመምህር፣ ርዕሰ-መምህር፣ ምክትል ርዕሰ-መምህር ወይም ሱፐርቫይዘር ዝውውር የሚታየው በትመሳሳይ ሙያ ማለትም (መምህር ከመምህር፣ ርዕሰ-መምህር ከርዕሰ መምህር፣ ምክትል ርዕሰ-መምህር ከምክትል ርዕሰ-መምህርና ሱፐርቫይዘር ከሱፐርቫይዘር ይሆናል፤

5/ ትምህርት በሚሰጥባቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች የሚያስተምሩ መምህራን ዝውውር ለመሙላት በአፍ መፍቻ ቋንቋው ተምረው የተመረቁ ወይም በአፍ መፍቻ ቋንቋው እያስተማሩ ያሉ መሆን አለባቸው፤

6/ ዝውውሩ በሚሰራበት ወቅት የአሰራር ቅደም ተከተሉ የትምህርት እርከንን በተመለከተ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድሚያ ይሰራል፤ በመቀጠል የመካከለኛ ደረጃ የሚሰራ ሲሆን በሶስተኛ ደረጃ የአንደኛ ደረጃ ይሆናል፡፡ በውጤት እኩል ከሆኑ እንደቅደም ተከተላቸው ለአካል ጉዳተኞችና ለሴቶች ቅድሚያ የሚሰጥ ሆኖ በቀጣይነት ደግሞ በተቧሚነት ወይም ተመራጭነት፣ በጋብቻ እና በአገልግሎት ቅደም ተከተል መሠረት ይሆናል፤

7/ በወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ደረጃ ለሚሰራው የትምህርት ቤት ትምህርት ቤት የመምህራን ዝውውር ተመሳሳይ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው መምህራን ክምችት እንዳይፈጠር ዝውውሩ ከትምህርት ቤቶች በቀረበው ፍላጎት መሰረት በወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም ክፍለ-ከተማ ተረጋግጦ የሚሰራ ይሆናል፤

8/ ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 6 የተሰጠው ስሌት እና የአፈጻጸም ሂደት ከትምህርት ቤት ትምህርት ቤት፣ ከጉድኝት ጉድኝት፣ ከወረዳ ወረዳ እንዲሁም ከዞን ዞን ለሚሰራ ዝውውር የሚያገለግል ይሆናል።

8. **ዝውውር የሚታይባቸው ምክንያቶች፤**

1/ የመምህራን፣የርዕሰ መምህራን፣ የምክትል ርዕሰ መምህራንና የሱፐርቫይዘሮች ዝውውር የሚታይባቸው ምክንያቶች አገልግሎት፣ ጋብቻ፣ ተመራጭነት ወይም ሹመት፣ ማህበራዊ ችግርና የጤና ችግር ናቸው፤

2/ በአገልግሎት ምክንያት የሚፈፀም የዝውውር፤

ሀ) መምህራን፣ ርዕሰ-መምህራን፣ ምክትል ርዕሰ-መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ከሚሠሩበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም ክፍለ ከተማ ወይም ትምህርት ቤት ወይም ጉድኝት ማዕከል ወይም ዞን ወይም ብሔረ-ሰብ አስተዳደር ወይም ሪጂዮ- ፖሊታን ከተማ የትዳር አጋራቸው ወደሚገኝበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም ክፍለ ከተማ ወይም ዞን ወይም ብሔረሰብ አስተዳደር ወይም ሪጂዮ ፖሊታን ከተማ ዝውውር ለማግኘት የራሳቸውን አገልግሎት መሠረት በማድረግ ተወዳድረው ብልጫ ሲኖራቸው ይሆናል፤

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ ሀ) በተጠቀሰው መሠረት በሚደረግ ውድድር እኩል አገልግሎት ካላቸው ቅድሚያ ለአካል ጉዳት ይሰጣል፤ ይህም ሆኖ እኩል ከሆኑ

ቅድሚያ ለሴት ይሰጣል፤ ይህም ሆኖ እኩል ከሆኑ ቅድሚያ ለሽመት ይሰጣል፤ ይህም ሆኖ እኩል ከሆኑ ቅድሚያ ለጋብቻ ይሰጣል፤ ይህም ሆኖ እኩል ከሆኑ ቅድሚያ ለቦታ ምርጫ ይሰጣል፤ ይህም ሆኖ እኩል ከሆኑ በዕጣ ይለያል፤

ሐ) ዝውውር ጠያቂ መርሱ በሚሰሩበት ትምህርት ቤት በአካል በመቅረብ መመላት አለባቸው፡፡ ሆኖም በትምህርት ቤት ደረጃ ዝውውር ለመመላት ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካጋጠመ ዝውውር ለማስሞላት ህጋዊ ውክልና በተሰጠው የወረዳ ወይም የከተማ አሰተዳደር ባለሙያ አመች ነው ተብሎ በተመረጠ ቦታ በአካል በመቅረብ በወቅቱ መመላት ይጠበቅባቸዋል፡፡

መ) ሕጋዊ ውክልና በሌለው አካል የሚሞላ የዝውውር ቅጽ ወይም መርሱ በፊርማቸው ሳያረጋግጡ ወደ ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም ክፍለ-ከተማ ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች ተሞልቶ የሚላክ ቅጽ ተቀባይነት የለውም፤ ለውድድርም አይቀርብም፡፡ በፍትሕ አካላት በተሰጠ ውክልና ዝውውር የሚሞላ ከሆነ የውክልና ወረቀቱ የዝውውር ቅጹ ሲሞላ ተያይዞ ለትምህርት ቤቱ መቅረብ አለበት፤

ሠ) በትምህርት ቤት ደረጃ ዝውውር ፈላጊዎች የሞሉት ቅጽ ትክክል ስለመሆኑ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር በፊርማው በማረጋገጥ እና የትምህርት ቤቱን ማህተም በማሳረፍ ለወረዳ ወይም ለከተማ አስተዳደሩ ወይም ለክፍለ-ከተማው ትምህርት ጽህፈት ቤት የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች ልማት ቡድን ማስረከብ ይጠበቅበታል፤

ረ) አንድ መምህር፣ ርዕሰ -መምህር፣ ምክትል ርዕሰ- መምህር ወይም ሱፐርቫይዘር መስፈርቶችን ሲያሟላ በየዓመቱ የዝውውር ፎርም የመመላት እና የመወዳደር መብት ይኖረዋል፤

ሰ) በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ (ረ) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከመደበኛ ዓመታዊ ዝውውር በኋላ በማንኛውም ጊዜ በአዲስ ቅጥር ተፈፅሞላቸው ጊዜያዊ የሥራ ቦታ ምደባ የተሠጣቸው መርሱ በመደበኛ ዝውውር ወቅት በክልል፣ በዞን፣ በብሔረ-ሰብ አስተዳደር፣ በወረዳ እና በከተማ አስተዳደር ደረጃ በቅደም ተከተል ለተቋቋመው የመርሱ ዝውውር ኮሚቴ ቋሚ የሥራ ቦታ ምደባ እንዲሠጣቸው የቦታ ምርጫቸውን በመለየት የዝውውር ፎርም በመመላት ማመልከት አለባቸው፤ ሆኖም፣ የሞሉትን ምርጫ በውድድር ማግኘት ካልቻሉ ወይም በራሣቸው ፈቃድ የዝውውር ፎርም ሞልተው የቦታ ውድድር ምርጫቸውን ለማሣወቅ ፈቃደኛ ካልሆኑና ካልሞሉ በየደረጃው ያለው የመርሱ ዝውውር ኮሚቴው በማንኛውም ጊዜ ያለምንም ቅድመ-

ሁኔታ በራሱ ተነሣሽነት ከአቻዎቻቸው ጋር በማወዳደር በጊዜያዊነት ከተመደቡበት የሥራ ቦታ በማንሣት በክልሉ ውስጥ በተገኘ ማንኛውም ክፍት የሥራ ቦታ በማዛወር ቋሚ የሥራ ቦታ ምደባ የሚሠጣቸው ይሆናል፡፡

ሸ) ለኑሮ አስቸጋሪ ተብለው በምድብ ስድስት በተቀመጡ ወረዳዎች በመሥራት ላይ ያለ መርሡ በአንድ ዓመት አገልግሎት የወረዳ-ወረዳ ዝውውር መሙላት ይችላል፤

ቀ) የክልል ክልል ዝውውር ለማግኘት በክልሉ ውስጥ የሰጠው አገልግሎት እስከ ሰኔ 30 ሦስት ዓመት ሊሞላው ይገባል፤

በ) አካባቢውን ለመልቀቅ የሚያስገድድ ችግር ካልተፈጠረ በስተቀር በግል ማመልከቻ ያለወቅቱ የሚቀርብ የዝውውር ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም፤

ተ) ዝውውር እንዲሰራለት ፎርም የሞላ መርሱ ሃሳቡን በመቀየር ዝውውር እንዲሰረዝለት የሚፈልግ ከሆነ በክልል ደረጃ የሚከናወነው ዝውውር ለመጀመር አንድ ቀን እስኪቀረው ድረስ ባለው ጊዜ በየደረጃ ዝውውሩን ለሚሰራው ኮሚቴ በማቅረብ የሞላው ዝውውር የሚሰረዝለት ይሆናል፡፡ ሆኖም በትኩ አዲስ የዝውውር ኮድ መሙላት አይችልም፤

3/ **በጋብቻ ምክንያት የሚፈጸም ዝውውር**

ሀ) ባልና ሚስት የዝውውር ጥያቄ ከማቅረባቸው አስቀድሞ ጋብቻ የፈጸሙ ለመሆናቸው የዝውውር ፎርም ከመሙላታቸው ከአንድ ዓመት በፊት የተረጋገጠ ሕጋዊ የጋብቻ ማስረጃ ያላቸው መሆኑ በወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤቶች ወይም ከተማ አስተዳደሮች ወይም ክፍለ-ከተማ የመምህራን ወይም የርዕሰ-መምህራን ወይም የምክትል ርዕሰ መምህራንና የሱፐርቫይዘር ማህደር ውስጥ መገኘት ይኖርበታል፤

ለ) ባል ወይም ሚስት መምህር፣ ርዕሰ መምህር፣ ምክትል ርዕሰ መምህር፣ የአገልግሎት ስሌቱ ለሚሰሩበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም ክፍለ ከተማ የተሰጠውን የቦታ ስሌት መሠረት ያደረገ ይሆናል፤

ሐ) ባል ወይም ሚስት ከትምህርት ሴክተር ውጭ የሌላ መሥሪያ ቤት ባልደረባ ከሆነ ቋሚ ሰራተኛ መሆናቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ከሚ/ትሠራበት መሥሪያ ቤት ማቅረብ ይጠበቅበ/ባታል፤

መ) በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ ባለትዳሮችን ለማቀራረብ ወይም አንድ ላይ እንዲሰሩ ለማድረግ ለጋብቻ በተሰጠው 15% ኮታ መጠቀም የሚቻለው በጋብቻ ምክንያት ዝውውር እንዲሰራለት የጠየቀው አካል ባለው የራሱ የተናጠል አገልግሎት ብቻ ነው፤

ሠ) በአንድ ትምህርት ቤት ወይም በአንድ ሪጂዮ -ፖሊታን ከተማ ወይም በአንድ ከተማ-አስተዳደር ወይም በአንድ ወረዳ በመሥራት ላይ ያሉ ባለትዳር መርሱ ወደ ሌላ ዞን ወይም ብሔረ-ሰብ አስተዳደር ወይም ሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ ወይም ከተማ-አስተዳደር ወይም ትምህርት ቤት ለመዛወር በዝውውር ፎርሙ ላይ ባለትዳር መሆናቸውን የሚገልጽ መረጃ ተሞልቶ ከተገኘ በሚኖራቸው አማካይ አገልግሎት አንድ ላይ እንዲዛወሩ ይደረጋል፤

ረ) በአንድ ትምህርት ቤት ወይም በአንድ ሪጂዮ-ፖሊታን ወይም በአንድ ከተማ አስተዳደር ወይም በአንድ ወረዳ በመስራት ላይ ያሉ ባለትዳር መርሱ ወደ ሌላ ዞን ወይም ብሔረሰብ አስተዳደር ወይም ሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ ወይም ከተማ-አስተዳደር ወይም ወረዳ ለመዛወር በዝውውር ፎርሙ ላይ ባለትዳር መሆናቸውን የሚገልጽ መረጃ ተሞልቶ ከተገኘ ዝውውሩ በተናጠል አይታይም፡፡ ሆኖም የጋብቻ ማስረጃቸው ከፋይላቸው ላይ ቢኖርም በዝውውር ፎርሙ ላይ ባለትዳር መሆናቸውን ካልሞሉ ለጋብቻ በተሰጠው ኮታ መወዳደር አይችሉም፡፡

ሰ) በአንድ ትምህርት ቤት ወይም በአንድ ክፍለ-ከተማ ወይም በአንድ ከተማ አስተዳደር በመሥራት ላይ ያሉ ባለትዳር መርሱ በፋይላቸው ላይ ባለትዳር መሆናቸውን የሚገልጽ ማስረጃ የታሰረ ቢሆንም ወደ ሌላ ዞን ወይም ብሔረሰብ አስተዳደር ወይም ሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ ወይም ከተማ-አስተዳደር ወይም ክፍለ-ከተማ ለመዛወር በዝውውር ፎርሙ ላይ ባለትዳር መሆናቸውን ካልሞሉ ለጋብቻ በተሰጠው ኮታ በመወዳደር ዝውውር አይሰራላቸውም፡፡

4/ በተመራጭነት ወይም በሹመት የሚፈፀም ዝውውር፡-

ሀ) በየደረጃው በሚፈፀም የመምህራን ማህበር ምርጫ ለማህበሩ አመራርነት የተመረጡ መምህራን ከሚሰሩበት ትምህርት ቤት ወደ ተመረጡበት ወረዳትምህርት ጽህፈት ቤት ወይም ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት ወይም ዞን ትምህርት መምሪያ ወይም ብሔረ-ሰብ አስተዳደር ወይም ሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ ወይም ክልል የምርጫው ዘመን እስኪጠናቀቅ ድረስ ተዛውረው እንዲሰሩ ይደረጋል፤

ለ) የወረዳ መምህራን ማህበር ተመራጮች በወረዳው ርዕሰ ከተማ ባሉት ትምህርት ቤቶች፣ የዞን መምህራን ማህበር ተመራጮች በዞኑ ወይም በብሔረ-ሰብ አስተዳደሩ ርዕሰ ከተማ ስር ባሉ ትምህርት ቤቶች፣ የክልሉ መምህራን ማህበር በክልሉ ርዕሰ ከተማ ስር ባሉት ትምህርት ቤቶች እንዲመደቡ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ያልተጠበቀ የመምህራን ክምችት የሚፈጥር ሆኖ ከተገኘ ከማስተማር ስራ ነጻ ከሆኑ ተመራጮች

በስተቀር ቀሪ ተመራጮች ለተወሰነ ጊዜ የሙያ ስራቸውን ለማከናወን በማያስችግራቸው በከተማ ዙሪያ ባሉ ትምህርት ቤቶች ሊመደቡ ይችላሉ፤

ሐ) በተኟሚነትም ሆነ በተመራጭነት የተሣወሩ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች ባለቤታቸው ከተመራጭነት ወይም ከተኟሚነት ሲነሱ ከባለቤታቸው ጋር አብረው ወይም ተቀራርበው መኖር በሚችሉበት አካባቢ በአገልግሎታቸው ተወዳድረው በሚመጥናቸው ዞን ወይም ብሔረ-ሰብ አስተዳደር ወይም ሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ ትምህርት መምሪያ ወይም ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት ስር ባሉ ትምህርት ቤቶች ይመደባሉ፤

መ) የዞን ወይም የክልል መምህራን ማህበር ተመራጮች በተመረጡበት የበጀት ዘመን ይሰሩበት ከነበረው ወይም ከተመረጡበት ወረዳ ደመወዛቸው እንዲከፈል ይደረጋል። ከቀጣዩ የበጀት ዘመን ጀምሮ የምርጫ ዘመን እስኪጠናቀቅ ድረስ ተመድበው የሚሰሩበት የከተማ ወይም ወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት በጀት ተይዞ እንዲከፈል ይደረጋል፤

ሠ) የራሳቸው ርእሰ ከተማ ከሌላቸው ወረዳዎች የሚመረጡ የማሕበር አመራሮች ደመወዝ ከተመረጡበት ወረዳ የሚከፈል ሆኖ የማስተማር ሥራ አመዳደባቸው በዚሁ አንቀጽ በፊደል ተራ ቁጥር ለ) መሠረት ይሆናል፤

ረ) አንድ ተመራጭ ሦስት ዓመት ሳይሞላው በምርጫ ካገኘው ሃላፊነት ቢነሳ በተነሳበት ወቅት ባለበት ቦታ በጊዚያዊነት ተመድቦ በመደበኛ የዝውውር ወቅት ዝውውር ሞልቶ እንዲወዳደር ይደረጋል። በዝውውር ወቅት የሞላውን ቦታ ካላገኘ ወደ ነበረበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት ተመልሶ እንዲሰራ ይደረጋል፤

ሰ) አንድ ተኟሚ ሦስት ዓመት ሳይሞላው በሹመት ካገኘው ኃላፊነት የሚነሳ ከሆነ በሹመት በተሰጠው ስሌት ዝውውር የተሰራለት መምህር ወይም ርዕሰ-መምህር ወይም ምክትል ርዕሰ-መምህር ወይም ሱፐርቫይዘር ከተኟሚነት በተነሳበት ወቅት ባለበት ቦታ በጊዚያዊነት ተመድቦ በመደበኛ የዝውውር ወቅት ዝውውር ሞልቶ እንዲወዳደር ይደረጋል፤ በዝውውር ወቅት የሞላውን ቦታ ካላገኘ ወደ ነበረበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት ተመልሶ እንዲሰራ ይደረጋል፤

ሸ) አንድ ተመራጭ የሁለት ዙር የምርጫ ጊዜውን አጠናቆ እንደገና ካልተመረጠ እንደማንኛውም መርሱ የዝውውር ፎርም ሞልቶ በጠየቀበት ዝውውር ካገኘ በተሣወረበት ወረዳ ስራውን ይቀጥላል። በጠየቀበት ዝውውር ካላገኘ በአመራርነት

ባገለገለበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት ወይም ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት ቋሚ ምደባ ይሰጠዋል፤

5/ በማሕበራዊ ችግር ምክንያት የሚፈፀም ዝውውር፤

በማህበራዊ ችግር ምክንያት የሚፈጸም ዝውውር ችግሩ በተፈጠረበት ወቅት የሚታይ ሲሆን አፈጻጸሙም እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) መርሱ በማህበራዊ ችግር ምክንያት ከሚሰራበት ቦታ ወደ ሌላ ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ዝውውር ለመስራት በዞን ፍትህ አካላት(**የፖሊስ ወንጀል ምርመራ ክፍል እና አቃቢ ህግ)** የተጣራ ማስረጃ ማቅረብ የሚጠበቅ ሲሆን ማስረጃው ከቦታው ካልተነሳ ለህይወቱ አስጊ የሆነና ወረዳው ወይም ከተማ-አስተዳደሩ ሊከላከልለት የማይችል መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ በፖሊስ መምሪያ ኃላፊው እና በአቃቢ ህግ ኃላፊው የተፈረመበት ሊሆን ይገባል፤ ዝውውሩም በዞን ትምህርት መምሪያ የዝውውር ኮሚቴ የሚከናወን ይሆናል፤

ለ) መርሱ በማህበራዊ ችግር ምክንያት ከሚሠራበት ትምህርት ቤት ወይም ጉድኝት ማዕከል ወደ ሌላ ጉድኝት ማዕከል ወይም ትምህርት ቤት ዝውውር ለመሥራት በወረዳ ፍትሕ አካላት የተጣራ ማስረጃ ማቅረብ የሚጠበቅ ሲሆን ማስረጃው ከቦታው ካልተነሳ ለህይወቱ አስጊ የሆነና በቀበሌ ደረጃ የሚገኘው የጸጥታ አካል ማህበራዊ ችግሩን ሊከላከልለት የማይችል መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ በወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ጽህፈት ቤት ኃላፊው ወይም በወረዳ ዐቃቤ ሕግ ኃላፊ ተፈርሞበት የቀረበ ሊሆን ይገባል፤ ዝውውሩም በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር የዝውውር ኮሚቴ የሚከናወን ይሆናል፤

ሐ) በዚህ ንኡስ አንቀጽ ፊደል ተራ ሀ) እና ለ) የቀረበውን ማስረጃ መሠረት በማድረግ ዝውውር የሚሠራው አካል ከችግሩ ነጻ ሊያደርገው በሚችልና ከሚነሳበት ትምህርት ቤት ወይም ጉድኝት ማዕከል ወይም ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት ጋር እንደቅደም ተከተሉ በመሠረተ ልማትና ለኑሮ ያለው ምቹነት ተመሳሳይ በሆነና ከነበረበት አካባቢ በመልካምድራዊ አቀማመጥ ተቃራኒ ነው ብሎ በሚያምንበት ትምህርት ቤት ወይም ጉድኝት ማዕከል ወይም ወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት ወይም ከተማ አሥተዳደር ትምህርት ጽሕፈት ቤት በጊዚያዊነት ሊመድበው ይችላል፡፡ ምደባው በሚሠራበት ወቅትም፡

1) የዞን ትምህርት መምሪያዎች ወይም የብሔረ-ሰብ ትምህርት መምሪያዎች በዞኑ ወይም በብሔረ-ሰብ አሥተዳደሩ ውስጥ የሚገኙ ወረዳዎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች የተፈጠረውን ችግር በመረዳት በዞኑ ወይም በብሔረ-ሰብ አሥተዳደሩ ውስጥ በሚገኙ ወረዳዎች ወይም ከተማ አሥተዳደሮች ምደባ ይሠጣሉ፤

2) የብሔረ-ሰብ አሥተዳደር ትምህርት መምሪያዎች በብሔረ-ሰብ ዞን አስተዳደሩ ስር በሚገኙ ወረዳዎች ወይም ከተማ አሥተዳደሮች የተፈጠረን ችግር በመረዳት በብሔረ-ሰብ አስተዳደሩ ስር ባሉ ወረዳዎች ወይም ከተማ አሥተዳደሮች ይመድቡታል፤

3) በሪጂዮ-ፖሊታን ትምህርት መምሪያ ባለ ክፍለ-ከተማ የተከሰተን ማህበራዊ ችግር በሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ ፍትህ አካላት ተጣርቶ ከቦታው ካልተነሳ ለሕይወቱ አስጊ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ በፖሊስና በአቃቢ ህግ ኃላፊዎች ተረጋግጦ የሚቀርብ ከሆነ የክልሉ ትምህርት ቢሮ የዝውውር ኮሚቴ በመሰረተ ልማትና ለኑሮ ያለው ምቹነት ተመሳሳይ ወደ ሆነ ሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ ትምህርት መመሪያ ይመድበዋል፡፡ ምደባውም በክልል ትምህርት ቢሮ የዝውውር ኮሚቴ አማካኝነት ይፈጸማል፤

መ) ለመኖር አሥቸጋሪ ሁኔታ በመፈጠሩ ምክንያት የተሰጠው ምደባ የዘመኑ የዝውውር ፎርም ከመሞላቱ በፊት ከሆነ ዝውውር የመመሥላት መብቱ የተጠበቀ ይሆናል፤ የመደበኛ ዝውውር ፍላጎት ማሳወቂያ ቅጹ ላይ የሞላ እና በፊርማው አረጋግጦ ለመኖር አስቸጋሪ ሁኔታ ተፈጥሮ ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ወይም ክፍለ- ከተማ ወይም ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት የተዛወረ መርሲ መደበኛ ዝውውር በሚሰራበት ወቅት ዝውውሩ የሚታይለት ሆኖ የቦታ ስሌት ማባዣ ነጥቡ በአስገዳጅ ሁኔታ ከመዛወሩ በፊት በነበረበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር በተሰጠው ስሌት መሠረት ይሆናል፤

ሠ) መርሲ በማሕበራዊ ችግር ምክንያት ከሚሠራበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም ክፍለ-ከተማ እንዲወጣ የሚያስገድድ ከሆነና የወረዳው ወይም የከተማ አስተዳደሩ ወይም የክፍለ ከተማው አስተዳደር ምክር ቤት በማሕበራዊ ችግር ምክንያት ዝውውር እንዲሠራ የበጀት ዓመቱን ደመወዝ (እስከ ሰኔ 30 ለመክፈል ፈቃደኝነቱን በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፤ የወረዳዎች ወይም የከተማ አስተዳደር

ወይም የክፍለ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤቶች የዓመቱን ደመወዝ ለመክፈል ፈቃደኛ ባልሆኑበት በማሕበራዊ ችግር ምክንያት ዝውውርም ሆነ ምደባ አይሰራም፡፡

6/ **በጤና ችግር ምክንያት የሚፈፀም ዝውውር፤**

መርሱን ከሚሠሩበት ቦታ በማንሳት ህክምናቸውን እየተከታተሉ ከህመማቸው ማገገም እንዲችሉ ህክምና ወዳለበት ተቋም በጊዜያዊነት የሚመደቡ ሲሆን አፈጻጸሙም፡-

ሀ) በሃኪሞች ቦርድ በሚሰጥ የህክምና ማስረጃ መሠረት በወረዳው ወይም በከተማ አስተዳደሩ ወይም በክፍለ-ከተማው ውስጥ በሚገኝ የጤና ተቋም ህክምናቸውን እንዲከታተሉ የወረዳው ወይም የክፍለ ከተማው ወይም የከተማ አስተዳደሩ የዝውውር ኮሚቴ ከሚሠሩበት ትምህርት ቤት በማንሳት ህክምና ወዳለበት ትምህርት ቤት ወይም ተመላልሰው መታከም የሚችሉ ከሆነ ለህክምና ተቋሙ ቅርብ በሆነ ትምህርት ቤት በጊዜያዊነት ይመድባቸዋል፤

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ ሀ) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የህክምና ወረቀታቸውን ለሁለተኛ ጊዜ የሚያሳድሱ ከሆነ በመደበኛ ዝውውር ወቅት በትምህርት ቤቱ ቋሚ ምደባ ይሰጣቸዋል፤

ሐ) መርሱ በሚሰሩበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም ክፍለ ከተማ የህክምና ተቋም ከሌለ በዞኑ ወይም በብሔረ-ሰብ አስተዳደሩ በሚገኙ ወረዳዎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች በሚገኙ የህክምና ተቋማት ወይም ለህክምና ተቋሙ ቅርብ በሆነ ወረዳ ወይም ከተማ አሥተዳደር ህክምናቸውን እንዲከታተሉ ይደረጋል፤

መ). በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ ሐ) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ መርሱ በሚሰሩበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም ክፍለ ከተማ የህክምና ተቋም ከሌለ በሌላ ዞን ለሚገኝ የህክምና ተቋም ቅርብ በሆነ ወረዳ ወይም ከተማ አሥተዳደር ህክምናቸውን እንዲከታተሉ ይደረጋል፤

ሠ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ ሐ እና መ) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የጤና ተቋሙ ባለበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ባሉ ትምህርት ቤቶች ከፍተኛ የሆነ የሰው ሃይል ክምችት የሚኖር ከሆነና መርሱ ተመላልሰው መታከም የሚችሉ ከሆነ ለጤና ተቋሙ ቅርብ በሆነ ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ምደባ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

ረ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ ሐ እና መ) በተገለጸው መሠረት ተግባራዊ ለማድረግ መርሱ ሲሠሩበት የነበረው ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር እስከ ሰኔ 30 ያለውን ደመወዝ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆኑን በደብዳቤ ማሳወቅ አለበት፡፡ ዝውውሩን

የሚሠራው አካልም ባለበጀት ወረዳዎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች ችግሩን ተረድተው ደመወዝ እንዲከፍሉ የማግባባት ሥራ ያከናውናል፤ ሆኖም፣ በጀት ባልተፈቀደበት ሁኔታ በጤና ምክንያት መርሱን ከሚሠሩበት ቦታ ወደ ሌላ ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ማዛወር አይቻልም፤

ሰ) መምህራን ወይም ርዕሰ-መምህራን ወይም ምክትል ርእሰ-መምህራን ወይም ሱፐርቫይዘሮች ከፍተኛ የሆነ የጤና ችግር አጋጥሟቸው ወደ ስፔሻላይዝድ የህክምና ተቋም በመሄድ ህክምናቸውን እንዲከታተሉ ማድረግ የግድ ከሆነ በመምህራን የሥራ ስምሪት መመሪያ በተቀመጠው የህክምና ፈቃድ አሠጣጥ መሠረት በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ወይም በክፍለ-ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት አማካኝነት ተግባራዊ ይደረጋል፤

ሸ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ ሰ) በተገለጸው መሠረት መምህራን፣ ርዕሰ-መምህራን፣ ምክትል ርእሰ-መምህራን ወይም ሱፐርቫይዘሮች ከፍተኛ የሆነ የጤና ችግር አጋጥሟቸው ከዞኑ ውጭ በሚገኙ የህክምና ተቋማት ወዳለበት ፈቃድ ተሠጥቷቸው ህክምናቸውን የሚከታተሉ ከሆነ ፈቃዱን መስጠት ያለበት የሚሠሩበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም ክፍለ-ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት ይሆናል።

ክፍል አራት

የወረዳዎች አመዳደብና የአገልግሎት ነጥብ አሰጣጥ

9. የሥራ ቦታዎች አመዳደብና ነጥብ አሰጣጥ፤

1/ አንድ መምህር ወይም ርዕሰ መምህር ወይም ምክትል ርዕሰ መምህር ወይም ሱፐርቫይዘር ከሚሰራበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም ሪጂዮ -ፖሊታን ከተማ ወደ ሌላ ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም ሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ በዝውውር የቦታ ለውጥ ለማድረግ ከሚሰራበት ቦታ በተሰጠው የቦታ ነጥብ ስሌት ይሆናል።

2/ ከሌላ ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር በተሰጠው ነጥብ ተዛውሮ የመጣ መምህር፣ ርዕሰ -መምህር፣ምክትል ርዕሰ-መምህር ወይም ሱፐርቫይዘር የትምህርት ቤት ወይም የጉድኝት ምደባ ለማግኘት በትምህርት ቤት የቦታ ነጥብ ስሌት ስለሌለ ዝውውር ካገኘበት ወረዳ ካለ መርሱ ጋር የትምህርት ቤት ትምህርት ቤት ወይም የጉድኝት ጉድኝት ዝውውር የሚሰራለት በጥሬ አገልግሎት ብቻ ይሆናል። ሆኖም ሁለቱም ተጋቢዎች ዝውውር የተሰራላቸው አገልግሎታቸው ተካፍሎ ከሆነ በተመሳሳይ እስከ ትምህርት ቤት ድረስ ተፈጻሚ ይሆናል፤

3/ የቦታ ነጥብ አሰጣጥ ወረዳዎች ባላቸው የመሠረተ ልማት፣ የአየር ንብረትና የኑሮ ሁኔታ ታሳቢ ያደረገ ነው። አመዳደባቸውም እንደሚከተለው ይሆናል፤

ሀ) ምድብ አንድ፡-

ባህርዳር፣ ደሴ፣ ጎንደር፣ ደብረብርሃን፣ ደብረማርቆስ፣ ወልድያ፣ እንጅባራ፣ ከሚሴ፣ ደብረ ታቦር፣ ፍኖተ ሠላም፣ ደባርቅ፣ ወረታ፣ ዳንግላ እና ኮምቦልቻ ከተሞች፤

ለ) ምድብ ሁለት፡-

የዋግ'ኽምራ ብሔረ-ሰብ አስተዳደር ዋና ከተማን ጨምሮ ከዞን ከተሞች ውጭ የሆኑ ሌሎች የራሳቸው ትምህርት ጽህፈት ቤት ያላቸው የከተማ አስተዳደሮች ሆነው በምድብ አንድ፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስትና ስድስት ከተጠቀሱት የወረዳ እና የዞን ርዕሰ ከተማ ውጭ ያሉ የወረዳ ርዕሰ ከተሞችና ከተማ አስተዳደሮች፤

ሐ) ምድብ ሶስት፡-

የምእራብ ጎንደር እና የወልቃይት ጠገዴ ሴቲት ሁመራ ዞን ርዕሰ ከተሞች ፤ በምድብ አንድ፣ ሁለት፣ አራት፣ አምስትና ስድስት ከተጠቀሱት የወረዳ ርዕሰ ከተማ ውጭ ያሉ ወረዳዎች እንዲሁም ዛታ፣ አፍላ፣ ራያ ባላ፣ ማይጠብሪ፣ ምዕራብ ጠለምት እና ምስራቅ ጠለምት ወረዳዎች ናቸው።።

መ) ምድብ አራት፡-

በምድብ አንድ ፣ሁለት፣ሶስት፣አምስትና ስድስት ከተጠቀሱት ወረዳዎች ውጭ የሆኑ አካባቢዎች ማለትም በረኽት፣መሀል ሜይንት፣ አርጎባ፣ ዳውንት፣ ጅሌ ጥሙጋ፣ደዌ ሃረዋ ፣ ቀወት፣ ሚዳ-ወረሞ፣ ባቲ ዙሪያ፣ ሳይንት አጅባር፣መቀጣዋ፤

ሠ) ምድብ አምስት፡-

ከምድብ አንድ እስከ አራት ከተጠቀሱትና ከምድብ ስድስት ውጭ ያሉ ወረዳዎች ማለትም ግሼራቤል፣ ጃናሞራ፣ ዚገም፣ዝቋላ ፣ምስራቅ በለሳ፣ ምዕራብ በለሳ እና ኪንፋዝ በገላ፣

ረ) ምድብ ስድስት፡-

ከምድብ አንድ እስከ ምድብ አምስት ከተጠቀሱት ወረዳዎች ውጭ ያሉ ወረዳዎች ማለትም መተማ፣ ምዕራብ አርማጭሆ፣ በየዳ፣ ጠለምት፣ ጠገዴ ፣ ሠሃላ፣ አበርገሌ፣ቋራ፣ ጃዊ፣ ታች አርማጭሆ፣አዲአርቃይ፣ማዕከላዊ አርማጭሆ፣ አዳኝ አገር ጫቆ፣ ወልቃይት፣ ፣ጠገዴ፣ አውራ እና ቃብታ ሁመራ ፤

4/ ለወረዳዎች የተሰጠ ኮድና የተሰጣቸውን የቦታ ነጥብ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ወይም ቅጽ በዚህ መመሪያ በአባሪነት የተያያዙ ሲሆን የነጥብ አሰጣጥ ሂደቱ በአንቀጽ 10 ከተራ ቁጥር 1 እሰከ 3 በተገለጸው መሠረት ይከናወናል፡፡

10. **ለዝውውር የአገልግሎት ስሌት አፈፃፀም፤**

1/ የነጥብ አሰጣጡ ሊያገለግል የሚችለውና ስሌት ውስጥ የሚገባው በመምህርነት፣ በርዕሰ-መምህርነት፣ በምክትልርዕሰ-መምህርነት፣ በሱፐርቫይዘርነት የተሰራበት አገልግሎት ብቻ ሲሆን በሌላ የተሰራበት የቦታ ማባዣ ስሌት ውስጥ ሳይገባ ጥሬ አገልግሎቱ ብቻ የሚሰላ ይሆናል፤

2/ በክልሉ ውስጥ በመሥራት ላይ ያሉ መምህራን፣ ርዕሰ መምህራን፣ ምክትል ርዕሰ መምህራን፣ ሱፐርቫይዘሮች በሚሠሩበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም ሪጂዮ - ፖሊታን ከተማ ያላቸው አገልግሎት በሚከተለው የነጥብ አሰጣጥ መሠረት እየተሰላ ይፈጸማል፤

ሀ) ምድብ አንድ ማባዣው "1" ሲሆን ማባዣ ስሌት የለውም በመሆኑም በጥሬ አገልግሎት ብቻ ይሰራል፤

ለ) ምድብ ሁለት ማባዣው "1.1" ሲሆን ማባዣ ስሌቱ ለዕያንዳንዱ ዓመት ተጨማሪ አንድ ወር ታስቦ ዝውውሩ ይሰላል፤

ሐ) ምድብ ሶስት ማባዣው "1.2" ሲሆን ማባዣ ስሌቱ ለዕያንዳንዱ ዓመት ተጨማሪ ሁለት ወር ታስቦ ዝውውሩ ይሰላል፤

መ) ምድብ አራት ማባዣው "1.3" ሲሆን ማባዣ ስሌቱ ለዕያንዳንዱ ዓመት ተጨማሪ ሶስት ወር ታስቦ ዝውውሩ ይሰላል፤

ሠ) ምድብ አምስት ማባዣው "1.4" ሲሆን ማባዣ ስሌቱ ለዕያንዳንዱ ዓመት ተጨማሪ አራት ወር ታስቦ ዝውውሩ ይሰላል፤

ረ) ምድብ ስድስት ማባዣው "1.5" ሲሆን ማባዣ ስሌቱ ለያንዳንዱ ዓመት ተጨማሪ አምስት ወር ታስቦ ዝውውሩ ይሰላል፤

3/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ /ከፊደል ተራ ሀ እስከ ረ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአንድ ዓመት በታች ለሆነ ሽርፍራፊ አገልግሎት ተጨማሪ ወር ነጥብ አይሰጠውም፤

4/ ከላይ የተመለከተው ነጥብ የሚያገለግለው ለአንድ ጊዜ ብቻ ሆኖ በየዓመቱ ለሚደረገው ዝውውር መርሱ የሚኖራቸው የቦታ ስሌት ዝውውር ሲሞላ የሚሠሩበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም ሪጂዮ -ፖሊታን ከተማ በተሰጠው ነጥብ ይሆናል።

ክፍል አምስት

የዝውውር አፈጻጸምና ፈጻሚ አካላት

11. **የዝውውር ወቅትና አፈጻጸም፤**

1/ ከታህሳስ 30 እስከ ጥር 10 በትምህርት ቤት እና በጉድኝት ደረጃ የዝውውር መጠየቂያ ቅጽ በመምህራን፣ በምክትል ርዕሰ መመህራን፣ በርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ይሞላል፡

2/ በትምህርት ቤት ደረጃ የዝውውር መሙያ ቅጽ ከጥር 10 እስከ ጥር 15 ተጠናቅሮና ተረጋግጦ ለወረዳ መምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ቡድን ይላካል፤

3/ የወረዳ መምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ቡድን የወረዳ - ወረዳ፣ የዞን-ዞን እና የክልል- ክልል ዝውውር ጠያቂ መርሱ መረጃ በማጠናቀርና በማረጋገጥ ከጥር 15 እስከ የካቲት 30 ለዞን መምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ቡድን ይልካል፤

4/ የዞን መምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ቡድን የክልል ክልል እና የዞን ዞን ዝውውር በማጠናቀርና በማረጋገጥ እስከ መጋቢት 20 ለክልል መምህራንና የትምህርት አመራር ዳይሬክቶሬት ይልካል፤

5/ የክልል መምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ዳይሬክቶሬት የዝውውሩን ቅጽ አሞላል በማየት እስከ መጋቢት 30 ግብረ-መልስ ይልካል፤

6/ የዞን መምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ቡድን እስከ ሚያዚያ 20 ለክልል ትምህርት ቢሮ የመጨረሻ የዝውውር ቅጽ በሶፍት ኮፒ ያስረክባሉ፤

7/ ለትምህርት ቢሮ ከተላከው የዝውውር ቅጽ በኋላ ተሞልቶ የሚቀርብ ቅጽ ተቀባይነት አይኖረውም፤

8/ የክልል መምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ዳይሬክቶሬት የክልል - ክልል እና የዞን - ዞን የመምህር፣ የርዕሰ መምህር፣ የምክትል ርዕሰ መምህር እና የሱፐርቫይዘር ዝውውር በመስራት እስከ ግንቦት 18 ለዞን፣ ለብሔረ-ሰብ አስተዳርና ለሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ መምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ቡድን ያሳውቃል፤

9/ የዞን፣ የብሔረሰብ አስተዳደርና የሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ መምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ቡድን ከክልል በዝውውር የተላከለትን በማካተት የወረዳ ወረዳወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የክፍለ-ከተማ የመምህር፣ የርዕሰ-መምህር፣ የምክትል ርዕሰ-መምህር ወይም የሱፐርቫይዘር ዝውውር እስከ ግንቦት 30 በመስራት ለወረዳ ወይም ለከተማ አስተዳር ወይም ለክፍለ-ከተማ አስተዳደር መምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ቡድን ያሳውቃል፤

10/ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የክፍለ-ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት መምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ቡድን ከዞን፣ ከብሔረ-ሰብ አስተዳደር እና ከሪጂዮ -ፖሊታን ከተማ መምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ቡድን በዝውውር የተላከለትን በማካተት እስከ ሰኔ 20 የትምህርት ቤት-ትምህርት ቤት እና የጉድኝት-ጉድኝት ዝውውር በመስራት ለተዛወሩ መምህራን፣ ርዕሰ መምህራን፣ምክትል ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ያሳውቃል፤

11/ ትምህርት ቤቶች ለተዛወሩ መምህራን፣ ርዕሰ መምህራን፣ ምክትል ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች እስከ ሃምሌ 10 የተሟላ ክሊራንስና የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የተሰጣቸው ወይም ያልተሰጣቸው መሆኑን በመግለጽና በሙያ ማሻሻያ የተሰሩ ስራዎችን በማካተት መሸኛ በመስጠት ለወረዳ ወይም ለከተማ አስተዳደር ወይም ለክፍለ ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት ይልካሉ፤

12/ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የክፍለ- ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት መምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ቡድን ዝውውር ላገኙ መምህራን፣ ርዕሰ መምህራን፣ ምክትል ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች እስከ ሃምሌ 15 የተሟላ ክሊራንስና የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የተሰጣቸው ወይም ያልተሰጣቸው መሆኑን በመግለጽ የተሟላ መሸኛ ሠጥተው ይልካሉ፤

13/ በመምህር፣ ርዕሰ መምህር፣ ምክትል ርዕሰ መምህር ወይም ሱፐርቫይዘር የተሞላ የዝውውር ቅፅ የሚያገለግለው ለአንድ ዓመት ብቻ ነው፤

12. **ሌሎች ልዩ ልዩ የዝውውር ተግባራት እና ተያያዥ ጉዳዮች አፈጻጸም፤**

1/ አዲስ አበባንና ድሬዳዋ ከተማ መስተዳደርን ጨምሮ ከክልል ክልል የሚደረገው ዝውውር በዚህ መመሪያ መሠረት ይሆናል፤

2/ መምህራን በክረምት ተከታታይ ትምህርት /ኮርስ/ ወይም ተመሣሣይ ስልጠና በመጀመራቸው ምክንያት ወደ ሌላ ክልል፣ ዞን ወይም ወረዳ ወይም ትምህርት ቤት ከመዛወር አይታገዱም፤

3/ ከክልል ክልል ዝውውር የሚሰራላቸው መምህራን ተዛውረው የሚሄዱበትን ክልል በማስተማሪያ ቋንቋነት የሚሰጡ ትምህርቶችን ቋንቋ ማወቅ ይጠበቅባቸዋል፤

4/ በጀማሪ መምህርነት ተቀጥረው በመደበኛ ዝውውር ወቅት ቋሚ ምደባ የተሠጣቸው መምህራን ለቀጣይ በመደበኛ ዝውውር ወቅት ለመወዳደር ከተቀጠሩበት ቀን ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ሁለት ዓመት የሚሞላቸው ከሆነ በጀማሪ መምህርነት ከመቀጠራቸው በፊት ያላቸውን አግባብ ያለው አገልግሎት በመያዝ ዝውውር እንዲሞሉ ይደረጋል፤

5/ በዚህ አንቀጽ ተራ ቁጥር 4 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ያለው አገልግሎት ሳይኖራቸው በጀማሪ መምህርነት የተቀጠሩ መምህራን መደበኛ የዝውውር ፎርም ለመሙላት በክፍል ሦስት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ሰ) በተቀመጠው መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

6/ በዚህ አንቀጽ ተራ ቁጥር 4 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በጀማሪ መምህርነት ከመቀጠራቸው በፊት አግባብ ያለው አገልግሎት ኖሯቸው የዝውውሩ ፍላጎት ቅጽ በሚሞላበት ወቅት ፍላጎታቸውን አሳውቀው የሞሉትን ቦታ ያላገኙ መርሱ የዝውውር ኮሚቴው አገልግሎታቸውን መሰረት በማድረግ ባሉት ክፍት ቦታዎች ይመድባቸዋል፤

7/ በዚህ አንቀጽ ተራ ቁጥር 4 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በጀማሪ መምህርነት ከመቀጠራቸው በፊት አግባብ ያለው አገልግሎት ኖሯቸው የዝውውሩ ፍላጎት ቅጽ በሚሞላበት ወቅት ለመሙላት ፍላጎት የሌላቸው መርሱ የዝውውር ኮሚቴው ባሉት ክፍት ቦታዎች ይመድባቸዋል፤

8/ በትምህርት ቤት አመራርነት ተወዳድረው በወረዳ ወይም በክፍለ ከተማው ወይም በከተማ አስተዳደሩ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ጊዚያዊ ምደባ የተሰጣቸው የትምህርት ቤት አመራሮች በሚሠሩበት ወረዳ ወይም ክፍለ ከተማው ወይም ከተማ አስተዳደር ውስጥ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ወይም የጉድኝት ማዕከላት ቋሚ የሥራ ቦታ ምደባ እንዲሰጣቸው ዝውውር መሙላት ይጠበቅባቸዋል፤

9/ በዚህ አንቀጽ በተራቁጥር 8 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ዝውውሩ በሚሰራበት ወቅት በምርጫቸው አገልግሎታቸውን ታሳቢ በማድረግ ከሌሎች የትምህርት ቤት አመራሮች ጋር ተወዳደረው ቋሚ ምደባ ይሰጣቸዋል፤ ሆኖም የሞሉትን ምርጫ ማግኘት ካልቻሉ እርስ በዕርሳቸው አገልግሎታቸውን መሰረት በማድረግ ዝውውሩን በሚሰራው ኮሚቴ ቋሚ ምደባ ይሰጣቸዋል፤

10/ ከትምህርት ቤት አመራርነት ወደ ሹመት ተመድበው የነበሩ ሃላፊዎች ከሃላፊነታቸው ተነስተው መምህር ሁነው እንዲመደቡ የሚያስችል መመሪያ ካለ መደበኛ ዝውውር እስኪሰራ ድረስ በሚሰሩበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም ክፍለ-ከተማ ጊዚያዊ ምደባ ይሰጣቸዋል፤ ቋሚ የስራ ቦታ ምደባ እንዲሰጣቸው ዝውውር መሙላት ይጠበቅባቸዋል።ዝውውሩ በሚሰራበት ወቅት በምርጫቸው አገልግሎታቸውን ታሳቢ በማድረግ በሚሰሩበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም ክፍለ-ከተማ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ከመምህራን ጋር ተወዳድረው ቋሚ ምደባ ይሰጣቸዋል፤ ሆኖም

የሞሉትን ምርጫ ማግኘት ካልቻሉ አገልግሎታቸውን መሰረት በማድረግ ዝውውሩን በሚሠራው ኮሚቴ ቋሚ ምደባ ይሰጣቸዋል፤

11/ በትምህርት ቤት አመራርነት ሲሰሩ ቆይተው ከሃላፊነት የሚወርዱ የትምህርት ቤት አመራሮች ከፍተኛው የትምህርት ዝግጅት የትምህርት ቤት አመራርነት ቢሆንና በዝቅተኛው የትምህርት ደረጃ እንዲያስተምሩ መምህር ሁነው የሚመደቡ ከሆነ ዝውውራቸው የሚታየው በሚያስተምሩበት ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ይሆናል፤

12/ በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ወይም በሪጂዮ -ፖሊታን ከተማ ወይም በክፍለ-ከተማ ደረጃ በሚሰራ የትምህርት ቤት ትምህርት ቤት ዝውውር ወቅት ከሌላ ወረዳ ወይም ዞን ወይም ክልል በዝውውር የመጡ መምህራን የትምህርት ደረጃንና የትምህርት አይነትን መሰረት በማድረግ በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደሩ ወይም በሪጂዮ-ፖሊታን ከተማው ወይም በክፍለ- ከተማው ካሉ መምህራን ጋር እኩል ይወዳደራሉ፡፡ እንዲሁም የትምህርት ቤት አመራሮች የትምህርት ደረጃን መሰረት በማድረግ በወረዳው ወይም ከተማ አስተዳደሩ ወይም ክፍለ ከተማው ወይም በሪጂዮ-ፖሊታን ከተማው ካሉ የትምህርት ቤት አመራሮች ጋር እኩል ይወዳደራሉ፤

13/ መደበኛ ዝውውር ከተሰራ በኋላ የትምህርት ማሻሻል አድርገው በወረዳው ወይም በክፍለ ከተማው ወይም በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ጊዚያዊ ምደባ የተሰጣቸው መምህራን ቋሚ የሥራ ቦታ ምደባ እንዲሰጣቸው ዝውውር መመላት ይጠበቅባቸዋል፤ የትምህርት ደረጃንና የትምህርት ዓይነትን መሠረት በማድረግ በወረዳው ወይም በክፍለ ከተማው ወይም በከተማ አስተዳደሩ ካሉ መምህራን ጋር እኩል ተወዳድረው እንዲዛወሩ ይደረጋል፡፡ ይሁንና የዝውውር ፎርም እንዲሞሉ ተጠይቀው ለመመላት ፈቃደኛ ያልሆኑ መምህራን አገልግሎታቸውን መሠረት በማድረግ የዝውውር ኮሚቴው ባሉ ክፍት ቦታዎች ይመድባቸዋል፤

14/ በወረዳው ወይም በከተማ አስተዳደሩ ወይም በክፍለ-ከተማው በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የመምህር እጥረት ሲያጋጥም ክምችት ካለበት ትምህርት ቤት በማንሳት እጥረት ወዳለበት ትምህርት ቤት በጊዚያዊነት በመመደብ ችግሩን መቅረፍ ይቻላል፡፡ ምደባው በሚሰራበት ወቅት በሚፈለገው የትምህርት ደረጃ እና የትምህርት ዝግጅት ዝቅተኛ አገልግሎት ያለው እንዲነሳ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ከፍተኛ አገልግሎት ያለው ፈቃደኛ መምህር ካለ ቅድሚያ ይሰጠዋል፤ ይሁንና ከቋሚ የስራ ቦታቸው ተነስተው በጊዚያዊነት የተመደቡ መምህራን እስከ በጀት አመቱ መጨረሻ ብቻ እንዲሰሩ የሚገደዱ ቢሆንም የበጀት አመቱ ሲጠናቀቅ ወደነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ ይደረጋል፡፡ ወደ ነበሩበት ቦታ

ሲመለሱ ዝውውር እንዲሞሉ አይጠበቅም፤ ሆኖም በቋሚነት ከተመደቡበት ትምህርት ቤት ለመዛወር ከፈለጉ ዝውውር በሚሞላበት ወቅት ባሉበት ቦታ ሁነው ዝውውር የመሙላት መብታቸው የተጠበቀ ነው ፤

15/ በዚህ አንቀጽ በተራ ቁጥር 4 እስከ 14 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ዝውውሩ በሚሰራበት ወቅት ትምህርታቸውን ከዲፕሎማ ወደ መጀመሪያ ዲግሪ አሻሽለው በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመድበው የሚሰሩ የዲግሪ መምህራን ቢኖሩ ከሌላ ወረዳ ተዛውረው ከሚመጡ የዲግሪ መምህራን ጋር በመወዳደር ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ባለ ክፍት ቦታ በቋሚነት እንዲመደቡ ይደረጋል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ፍላጎት ባለመኖሩ መመደብ ካልተቻለ የዲፕሎማ መምህራን ዝውውር ከመሰራቱ በፊት በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አገልግሎታቸውን መሠረት በማድረግ ቋሚ ምደባ ይደረግላቸዋል፤

16/ በትምህርት ማሻሻል ምክንያት መምህራን ከሚሰሩበት ትምህርት ቤት ከፍ ያለ ደረጃ ወዳለው ትምህርት ቤት በጊዚያዊነት እንዲመደቡ የሚደረግ ከሆነ ትምህርት ካሻሻሉት መካከል ቅድሚያ በፍላጎት ከፍተኛ አገልግሎት ያለው/ያላቸው እንዲመደብ/ቡ ይደረጋል፤ሆኖም ግን በፍላጎት ከፍተኛ አገልግሎት ያለው/ያላቸው ለመሄድ ፈቃደኛ ካልሆነ/ኑ በሚፈለገው የትምህርት ደረጃ እና የትምህርት ዝግጅት ባለው ክፍት ቦታ መሰረት ዝቅተኛ አገልግሎት ያለው/ያላቸው እንዲመደብ/ቡ ይደረጋል፡፡

17/ በዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት አንቀጽ ሰባት ንዑስ አንቀጽ 1 እና 3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከሚፈለገው የትምህርት ደረጃ በታች ኖሯቸው በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅና በቴክኒካል ድሮዊንግ መምህርነት ተመድበው በመስራት ላይ ያሉ ዝውውራቸው ለደረጃው የሚፈለገውን የትምህርት ደረጃ ካሟሉት ጋር እኩል ይታያል፤

18/ በክፍል ሶስት አንቀጽ ሰባት በተራ ቁጥር 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሰርተፊኬት የትምህርት ዝግጅት ኖሯቸው ለዲፕሎማ ትምህርት በመማር ላይ ያሉ መምህራን ስልጠና በጀመሩበት የትምህርት አይነት ከዲፕሎማ መምህራን ጋር ዝውውራቸው እኩል ይታያል፡፡የሰርተፊኬት የትምህርት ዝግጅት ኖሯቸው በተለያየ ምክንያት ስልጠና ያልጀመሩ መምህራን በወረዳ ደረጃ በሚሰራው የትምህርት ቤት ትምህርት ቤት ዝውውር የሰርተፊኬት የትምህርት ደረጃ ካላቸው መምህራን ጋር በመወዳደር ዝውውር ሊታይላቸው ይችላል፤

19/ በውህድ /የተቀናጀ/፣ ስፔሻሊስትና ጀኔራሊስት ሞዳሊቲዎች የተመረቁ መምህራን ዝውውር ከሚያስተምሩት የክፍል ደረጃ እና ከተመረቁበት የትምህርት ዝግጅት አቻ/ቀረቤታ/ ካላቸው መምህራን ጋር ይታያል ፤

20/ በሦስት አብይ የትምህርት አይነት በዲፕሎማ ሊኒየር ሞዳሊቲ ተመርቀው በማስተማር ላይ ያሉ መምህራን ከተመረቁበት የትምህርት ዓይነት በመረጡት በአንዱ ብቻ የዝውውር ፎርም እንዲሞሉ ተደርጎ ተመሳሳይ የትምህርት ዓይነትና ደረጃ ካላቸው መምህራን ጋር ዝውውራቸው እኩል ይታያል፤

21/ በተለያየ የትምህርት ዓይነት ተመርቀው በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዜግነት ትምህርትን በማስተማር ላይ ያሉ መምህራን ዝውውር በሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት ተመርቀው የዜግነት ትምህርትን በማስተማር ላይ ካሉት መምህራን ጋር እኩል የሚታይ ይሆናል፤

22/ የሳተላይት ክፍሎች ምደባ በሚደረግበት ወቅት በጤና ችግር ምክንያት በልዩ ሁኔታ በጊዚያዊነት ከተመደቡት መምህራን ውጪ ያሉት መምህራን አመዳደብ በተመለከተ ትምህርት ቤቱ አንደኛ ደረጃ ብቻ ከሆነ እንደሚፈለገው የመምህር ብዛት በተፈለገው የትምህርት ዝግጅት ካሉት መምህራን መካከል ዝቅተኛ አገልግሎት ያለውን በመመደብ፤ ትምህርት ቤቱ ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ከሆነ 7ኛ ወይም 8ኛ ክፍል ከሚያስተምሩ መምህራን ውጪ እንደሚፈለገው የመምህር ብዛትና የትምህርት ዝግጅት ዝቅተኛ አገልግሎት ያለውን መምህር በመመደብ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

23/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 22 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከፍተኛ አገልግሎት ይዞ በሳተላይት ክፍሎች ለመመደብ ፍላጎት ያለው መምህር ቅድሚያ ይሰጠዋል፤

24/ በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የሰለጠኑ መምህራን ዝውውራቸው በትምህርት ደረጃ እና በትምህርት ዝግጅታቸው መሠረት ይሆናል፡፡ይሁንና ከሰርተፊኬት ወደ ዲፕሎማ የቅድመ አንደኛ ደረጃ መምህርነት የደረጃ ማሳደግ ሥልጠና የጀመሩ ከሆነ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 18 በተገለጸው መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

25/ በዲፕሎማ እና በመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ በልዩ ፍልጎት የትምህርት ዝግጅት ተመርቀው በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማስተማር ላይ ያሉ መምህራን የትምህርት ዝግጅትና አገልግሎታቸውን ብቻ መሠረት በማድረግ ዝውውራቸው ይታያል፤

26/ ዝውውር እንዲሰራለት ፍላጎቱን የሚያቀርብ መርሱ በትምህርት ቤት ደረጃ በተዘረጋው የተከታታይ የሙያ መሻሻያ መርሀ ግብር እየተሳተፈ መሆኑን ከትምህርት ቤት ርዕሰ

መምህሩን ወይም ከጉድኝት ሱፐርቫይዘሮች የጽሁፍ ማረጋገጫ ካልቀረበ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የክፍለ-ከተማ መምህራን ልማት ቡድን በተከታታይ ሙያ መሻሻያ መርሃ ግብር የማይሳተፈውን መርሱ ዝውውር በጽሁፍ እንዲሰረዝ ያደርጋል የተሞላው ፍላጎትም ለውድድርም አይቀርብም፤

27/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 26 የተመለከተው ቢኖርም፣ ትምህርት ቤቱ ወይም ጉድኝት ማዕከሉ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት የተዘጋ ከሆነና መርሱ ሥራ ላይ ካልሆኑ ተከታታይ ሙያ ማሻሻያ ሥልጠና መሳተፋቸውን የሚገልጽ ማስረጃ እንዲያቀርቡ አይገደዱም፤

28/ ከመደበኛ የመርሱ ዝውውር ውጭ በተናጠል የሚቀርብ የስምምነትም ሆነ የርስ በርስ ዝውውር ተቀባይነት አይኖረውም፤

29/ ዝውውር ከተፈጸመ በኋላ እንዲሰረዝ የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም.።

13. **በየደረጃው የሚገኙ ፈጻሚ አካላት ተግባርና ሃላፊነት፤**

1/ የክልል የመምህራንና የትምህርት አመራር ልማት ዳይሬክቶሬት ፡-የዚህን መመሪያ የዝውውር አፈጻጸም ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ ክፍተቶችን በመለየት ማሻሻያ ረቂቅ በማዘጋጀት መመሪያው እንዲሻሻል የማሻሻያ ሃሳብ ለቢሮው ያቀርባል፤

2/ የየዘመኑን የዝውውር ማስፈጸሚያ እቅድ ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅለት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

3/ የዞን- ዞን፣ የክልል- ክልል፣ የአዲስ አበባንና ድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር ዝውውር የሚሞሉ መምህራንና የትምህርትቤት አመራሮች መረጃ ያሰባስባል፣ ዝውውሩን ይፈጽማል፣ ዝውውር ያገኙትን መምህራንና የትምህርትቤት አመራሮችን ለዞንና ክልሎች ያሳውቃል፤

4/ የመምህራን፣ ርዕሰ-መምህራን፣ ምክትል ርዕሰ-መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ዝውውር በየደረጃው ባለው የትምህርት ቢሮ መዋቅር በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመፈጸም እንዲቻል የመረጃ ልውውጥ የሚጠናከርበትን መንገድ ያመቻቻል፤

5/ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ የሚቀርብ የዝውውር ቅሬታን ያስተናግዳል፣ ምላሽ ይሰጣል፣

6/ የመምህራንን፣ የትምህርት ቤት አመራሮችና ሱፐርቫይዘሮችን ዝውውር ለመሥራት የድርጊት መርሃግብር ያዘጋጃል፣ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ይሰጣል፤

7/ በመርሱ የዝውውር አፈጻጸም ሂደት ላይ ስህተት መፈጸሙን ጥቆማ ሲደርሰው ወይም ስህተት ተፈጽሞ ሲያገኘው ጉዳዩን በመመርመር ማስተካከያ ያደርጋል፤

8/ የዝውውር ኮሚቴ አባላት ከተለያዩ የቢሮው አደረጃጀት አካላት የተወጣጡ ሲሆን፤

ሀ) የክልሉ ትምህርት ቢሮ የመምህራንንና የትምህርትቤት አመራሮች ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር/ተወካይ------ ሠብሳቢ፣

ለ) ከክልሉ ትምህርት ቢሮ የመምህራንንና የትምህርትቤት አመራሮች ልማት ዳይሬክቶሬት 3 ባለሙያዎች------ አባላት፣

ሐ) ከክልል መምህራን ማህበር 3 አመራሮች ------- አባላት፣

መ) ከየዞኑ የመምህራን ልማት ቡድን አንድ አንድ ባለሙያ------ አባላት፣

ሠ) ከየዞኑ የመምህራን ማህበር አንድ አንድ ተወካይ------ አባላት፣ ናቸው።

14. **የዞን ወይም የብሔረ-ሰብ አስተዳደር ወይም የሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች ልማት ቡድን ተግባርና ሃላፊነት፡-**

1/ የመምህራንንና የትምህርት ቤት አመራሮችን የወረዳ ወረዳ ዝውውር ለመሥራት የድርጊት መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ይሰጣል፤

2/ በዝውውር መስፈርቱ ቅፅ መሠረት መረጃ መጠናቀሩን ያረጋግጣል፤

3/ የወረዳ-ወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የክፍለ ከተማ ዝውውርን ያከናውናል፣ በየደረጃው ዝውውር ያገኙትን መርሱ ዝውውራቸውን ለወረዳ ያሳውቃል፤

4/ የዞን ወይም የብሔረሰብ አስተዳደር ወይም የሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ የክልል - ክልል፣ አዲስ አበባንና ድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር ዝውውርን በመለየትና በማጠናቀር ለክልል ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅጽ በሀርድ እና በሶፍት ኮፒ ይልካል፤

5/ በሪጂዮ-ፖሊታን ከተማው የሚገኙ ክፍለ -ከተማዎች በሰው ኃይል ተሟልተው ሥራ እስኪጀምሩ ድረስ የክፍለ ከተማዎችን ሥራ ያከናውናል፤

6/ በዝውውር ምክንያት የሚቀርብ ቅሬታን በወቅቱ ያስተናግዳል፣ ምላሽ ይሰጣል፤

7/ የዝውውር ኮሚቴ አባላት ከወረዳዎች የተውጣጡ የመምህራን ልማት ቡድን ባለሙያዎችን እና የመምህራን ማሕበር ተወካዮች ያካተተ ሲሆን የኮሚቴው አባላትም፤

ሀ) የዞኑ ትምህርት መምሪያ የመምህራንንና የትምህርትቤት አመራሮች ልማት ቡድን መሪ/ተወካይ----------ሠብሳቢ፤

ለ) ከዞኑ ትምህርት መምሪያ የመምህራንንና የትምህርትቤት አመራሮች ልማት ቡድን 2 ባለሙያዎች ---------- አባላት፤

ሐ) ከዞን መምህራን ማህበር 2 አመራሮች ----------አባላት፤

መ) ከየወረዳ የመምህራን ልማት ቡድን አንድ አንድ ባለሙያ----------አባላት፤

ሠ) ከየወረዳው የመምህራን ማህበር አንድ አንድ ተወካዮች---------- አባላት፤ ናቸው።

15. **የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ወይም የክፍለ-ከተማ የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች ልማት ቡድን ተግባርና ሃላፊነት፡-**

1/ በክልሉ የመምህራንና የትምህርት አመራሮች ልማት ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀውን የዝውውር ቅፅ በማባዛት ለየትምህርት ቤቶች ያሰራጫል፡፡ ግንዛቤ እንዲያገበት ያደርጋል፤

2/ የወረዳ፣ የክፍለ-ከተማ፣ የከተማ አስተዳደር፣ የዞን ወይም የብሔረሰብ አስተዳደር ወይም የሪጂዮ-ፖሊታን፣ የክልል ክልል፣ የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ መስተዳድርን ዝውውር አጠናቅሮ ለዞን በሀርድ እና ሶፍት ኮፒ ይልካል፤

3/ ዝውውር እንዲሰራላቸው የጠየቁ መርሱ በትምህርት ቤት ደረጃ በሚሰጠው ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራም በመሳተፍ ላይ ያሉ መሆናቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ መኖሩን ያጣራሉ፤

4/ ያጉድኝት ሱፐርቫይዘሮችን ዝውውር ያስሞላል ለሚመለከተው አካልም ያሳውቃል፤

5/ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በትምህርት ቤት ደረጃ ዝውውር መመላት ካልተቻለ አመቺ በሆነው ቦታ ላይ ባለሙያ በመመደብ ዝውውር ማስሞላት፤

6/ በወረዳ ወይም በክፍለ-ከተማ ወይም በከተማ-አስተዳደር ውስጥ የትምህርት ቤት - ትምህርት ቤት እና የጉድኝት-ጉድኝት ዝውውር ያከናውናል፤

7/ በየደረጃው ለተዛወሩ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች ዝውውራቸውን ያሳውቃል፣ የተሟላ መሸኛና ፋይላቸውን ቆጥሮ በማሸግ በመሸኛ ወደ ተዛወሩበት ወረዳ ይልካል፤

8/ በዝውውር ምክንያት የሚቀርብ ቅሬታን በወቅቱ ያስተናግዳል፤ ምላሽ ይሰጣል፤ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

9/ የወረዳ ወይም የክፍለ-ከተማ ወይም የከተማ አስተዳደር መርሱ ዝውውር ከመምህራን ልማት ቡድን እና ከመምህራን ማህበር በተውጣጣ የዝውውር ኮሚቴ አባላት የሚከናወን ሆኖ አባላቱም ፤

ሀ) የወረዳ ወይም የክፍለ ከተማ ወይም የከተማ-አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት የመምህራንና የትምህርትቤት አመራሮች ልማት ቡድን መሪ/ተወካይ---------ሠብሳቢ፤

ለ) የወረዳ ወይም የክፍለ-ከተማ ወይም የከተማ-አስተዳደር ትምህርት ጽሕፈት ቤት የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች ልማት ቡድን ከ2 እስከ 3 ባለሙያዎች---- ----አባላት፤

ሐ) ከወረዳ ወይም ከክፍለ- ከተማ ወይም ከከተማ አስተዳደር መምህራን ማሕበር 2 አመራሮች ----------አባላት ናቸው፡፡

16. **የርዕሰ-መምህር ተግባርና ኃላፊነት፤**

1/ በተዘጋጀው የዝውውር ቅጽ መሰረት የመምህር፣ ርዕሰ መምህር፣ምክትል ርዕሰ መምህር ዝውውር በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተሞልቶ እንዲጠናቀቅ ያደርጋል፤

2/ መረጃውን በማጠናቀር በሀርድ እና ሶፍት ኮፒ ለወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት የመምህራንና የትምህር አመራሮች ልማት ቡድን ይልካል፤

3/ በትምህርት ቤቱ በመሥራት ላይ ያሉ መምህራን በተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራም በመሳተፍ ላይ ያሉ መምህራንን ብቻ የዝውውር ቅጽ በማስሞላት ለወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም ክፍለ-ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት የመምህራንና የትምህርት አመራሮች ልማት ቡድን ይልካል፤

4/ የተዛወሩ መምህራን፣ ርዕሰ መምህር፣ምክትል ርዕሰ መምህር በተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና የተሰሩ ስራዎችን ማህደረ ተግባር (portfolio) እንዲሁም የውጤት ተኮር እቅድ አፈፃፀም ምዘና ውጤት በማካተት የተሟላ መሸኛ በመስጠት ለወረዳ የመምህራንና የትምህርትቤት አመራሮች ልማት ቡድን ይልካል፤

5/ በዝውውር ምክንያት የሚቀርብ ቅሬታን በወቅቱ ያስተናግዳል፣ ምላሽ ይሰጣል።

17. **በየደረጃው በሚገኘው የሙያ ማህበር የሚወከሉ የመምህራን ማህበሩ አመራሮች ተግባርና ኃላፊነት፤**

የመምህራን፣ ርዕሰ መምህራን፣ ምክትል ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ዝውውር በሚሰራበት ወቅት በየደረጃው ከሚገኙት የመምህራንና የትምህርት አመራሮች ልማት ፈፃሚዎች እና በትምህርት ቤት ካለው አካል ጋር በጋራ ይሠራሉ፤ በትክክል መሰራቱን በፊርማቸው ያረጋግጣሉ።

ክፍል ስድስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

18. **ስለቅሬታ አቀራረብ፣ አወሳሰን እና ተጠያቂነት፤**

1/ በክልል ደረጃ የሚከናወነው መደበኛ ዝውውር ከተከናወነ በኋላ የሚቀርብ ቅሬታ ካለ የዝውውር ኮሚቴ አባል በሆኑት የክልል መምህራን ልማት ባለሙያዎች እና የክልል መምህራን ማህበር ተወካዮች እየተገናኙ ቅሬታውን ይፈታሉ፤

2/ በዞን ወይም በብሔረ-ሰብ አስተዳደር ወይም በሪጂዮ-ፖሊታን፣ ወይም በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ደረጃ የሚከናወነው መደበኛ ዝውውር ከተከናወነ በኋላ የሚቀርብ ቅሬታ ካለ የዝውውር ኮሚቴ አባል በሆኑት በዞን ወይም በብሔረ-ሰብ አስተዳደር ወይም በሪጂዮ -ፖሊታን ወይም በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር መምህራን ልማት

ባለሙያዎች እና በዞን ወይም በብሔረ-ሰብ አስተዳደር ወይም በሪጂዮ-ፖሊታን ወይም በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር መምህራን ማሕበር ተወካዮች እየተገናኙ ቅሬታውን ይፈታሉ፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በተሰጠው ምላሽ ቅሬታ ያለው ወገን ቅሬታውን በጽሁፍ በየደረጃው ለሚገኝ የቅሬታ ሰሚ አካል ዝውውሩ ይፋ ከሆነበት አንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሊያቀርብ ይችላል፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ቅሬታ የቀረበለት በየደረጃው የሚገኘው የዝውውር ኮሚቴ ከ10 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለቀረበው ቅሬታ በጽሁፍ መልስ መስጠት አለበት፤

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በተሰጠው መልስ አግባብ አይደለም የሚል ወገን ዝውውሩ በታየበት ደረጃ ማለትም (ለወረዳ ወይም ለከተማ አስተዳደር ወይም ለክፍለ-ከተማ ቅሬታ ሠሚ አካላት፣ ለዞን ወይም ለብሔረ-ሰብ አስተዳደር ወይም ለሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ ቅሬታ ሰሚ አካላት ፣ ለቢሮው ቅሬታ ሰሚ) መልስ ከተሰጠው 10 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በድጋሚ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል። የቅሬታ ሰሚ አካላትም በ5 ቀን ውስጥ ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ትምህርት ጽህፈት ቤቱን ወይም ትምህርት መምሪያውን ወይም ትምህርት ቢሮውን ለሚመራው ኃላፊ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል ኃላፊውም ጉዳዩን በመመርመር ውሳኔ ይሠጣል፤

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት በኃላፊው በሚሰጠው መልስ ቅሬታ ያለው ቅሬታ አቅራቢ የተሰጠውን መልስ በማደራጀት ለክልሉ የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፤

7/ ዝውውር ጠያቂ መምህራን፣ ርዕሳነ መምህራን፣ ምክትል ርዕሳነ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች በሞሉት የዝውውር ፎርም መሰረት ቅሬታ አቅርበው ቅሬታቸው ተገቢ ሆኖ ከተገኘ በፍጥነት የማስተካከያ ሥራ በየደረጃው መሠራት አለበት፤

8/ ዝውውር ከተፈጸመ በኋላ በየደረጃ ዝውውሩን በሚሞላው ኮሚቴ ስህተት ምክንያት ዝውውሩ ሲሰረዝ መርሱው ወደ ነበረበት ቦታ ይመለሳል፤ የነበረበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ወይም ሪጂዮ-ፖሊታን ከተማ የመቀበል ግዴታ ይኖርበታል፤

19. **ስለ ተጠያቂነት፤**

1/ ከትምህርት ቤት ጀምሮ በየደረጃው ዝውውሩን የፈፀመው አካል ወይም ግለሰብ ለፈፀመው የአሠራር ግድፈትና ጥፋት በዲስፕሊን የሚጠየቅበት አሠራር እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ባለው የወንጀልና ፍታብሄር ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፤

2/ ዝውውር ጠያቂ መምህር፣ ርዕሰ-መምህር፣ ምክትል ርዕሰ-መምህር ወይም ሱፐርቫይዘር በወቅቱ የሞሉት የዝውውር ፍላጎት ማሳወቂያ ቅጽ ትክክል ስለመሆኑ በፊርማቸው በማረጋገጥ ለወረዳ ወይም ለኩተማ አስተዳደር ወይም ለክፍለ-ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት ከተላከ በኋላ በዞን ወይም በብሔረ-ሰብ አስተዳደር ወይም በክልል ደረጃ በሚሰራ የመረጃ ማጠናቀር ሂደት ስህተት ቢፈጠር ስህተቱን የፈጠረው አካል ወይም ግለሰብ በየደረጃው በዲሲፕሊን፤በወንጀልና ፍታብሄር ሕግ መሠረት ይጠየቃል፤

3/ የሀሰት የህክምና ማስረጃ በማቅረብ ከደመወዝ ጋር የህመም ፈቃድ እንዲሰጠው ያደረገ ወይም የሀሰት የጋብቻ ሰርተፊኬት በማቅረብ ዝውውር እንዲሰራለት ያደረገ መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር የመረጃው ሀሰት መሆን ከተረጋገጠ የተሰራለት ዝውውር ወይም የተሠጠው የህመም ፈቃድ ተሰርዞ በዲሲፕሊን፤በወንጀልና ፍታብሄር ሕግ መሠረት ይጠየቃል፤

4/ ከወረዳ ጀምሮ እስከ ክልል የሚገኘው የመምህራንና ትምህርት ቤት አመራር ልማት ቡድን ወይም ዳይሬክቶሬት ከመምህራን ማህበር ጋር በመሆን በየደረጃው በሚፈጸም የዝውውር ሂደት ስህተት ወይም ጥፋት ተፈጥሮ ባገኘው ጊዜ ስህተቱን በማጣራት በማንኛውም ጊዜ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤ ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

5/ በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ወይም ልዩ መፍትሄ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ቢሮው ጉዳዩን በመመርመር ከዚህ መመሪያ ጋር በማይቃረን ሁኔታ አስተዳደራዊ መፍትሄ ሊሰጥ ይችላል።

20. **መመሪያውን ስለ ማሻሻል፤**

ቢሮው እንደ አስፈላጊነቱ ይህንን መመሪያ ሊያሻሽለው ወይም ሊሽረው ይችላል።

21. **ስለተሻሩ እና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች፤**

1/ "የመምህራን፣ የርዕሰ መምህራን፣ የምክትል ርዕሰመምህራንና የሱፐርቫይዘሮች የዝውውርና ምደባ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 01/2014 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፤

2/ ቢሮው ከፀጥታ፤ ማሕበራዊ እና የጤና ችግር ጋር ተያይዞ ለመርሱ ጊዜያዊ ዝውውር ማስፈፀሚያ በቁ.ት/በ6/37/ዕ-11 በቀን-21-12-2016 ዓ.ም ያስተላለፈው የጊዜያዊ ዝውውር ሠርኩላር ደብዳቤ እና ሌሎች ተመሣሣይ የዝውውር ማስፈፀሚያ ደብዳቤዎች፤ ውሣኔዎች በሙሉ በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፤

3/ ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ሌሎች መመሪያዎችና የተለመዱ አሰራሮች በዚህ መመሪያ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

22. **መመሪያው የሚፀናበትና አባሪዎች፤**

1. ከዚህ መመሪያ መጨረሻ አባሪ የተደረጉ ቅፅ-001 እና ቅፅ-002 የዚህ መመሪያ አካል ተደርገው የሚፈፀሙ ናቸው፤
2. ይህ መመሪያ በቢሮው ከፀደቀበት ህዳር-25/2018ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፤

የአብክመ ትም/ቢሮ

ህዳር-25/2018 ዓ.ም

ባህር ዳር

ተ.ቁ	ሪጅዮ ፖሊታን ከተማ አስተዳደር	ኮድ	ማስገ
1	ባህርዳር	1	የለውም
2	ጎንደር	2	የለውም
3	ደሴ	3	የለውም
4	ኮምቦልቻ	4	የለውም
5	ደብረብርሃን	5	የለውም
6	ደብረማርቆስ	6	የለውም
7	ደብረታቦር	7	የለውም
8	ወልድያ	8	የለውም

ተ.ቁ	ሰሜን ጎጃም 181	ኮድ	ማስገ
1	ሰሜን አቸፈር	9	1.2
2	ደቡብ አቸፈር	10	1.2
3	ባ/ዳር ዙሪያ	11	1.2
4	ይ/ዱንላ	12	1.2
5	ጎንጅ ቆለላ	13	1.2
6	ደቡብ ሜጫ	14	1.2
7	ሰሜን ሜጫ	15	1.2

ተ.ቁ	ወ/ጠ/ሰ/ሁመራ 182	ኮድ	ማስገ
1	ሰቲት ሁመራ ከ/አስ	16	1.2
2	ዳንሻ ከ/አስ	17	1.2
3	ጠገዴ	18	1.5
4	ቃብታ ሁመራ	19	1.5
5	አውራ	20	1.5
6	ወልቃይት	21	1.5

ተ.ቁ	ደቡብ ወሎ 183	ኮድ	ማስገ
1	አምባሰል	22	1.2
2	ወግዲ	23	1.2
3	ቦረና	24	1.2
4	ጃማ	25	1.2
5	ቃሉ	26	1.2
6	ከሳሳ	27	1.2
7	ኩታ በር	28	1.2
8	ለጋምቦ	29	1.2
9	መሃል ሳንይት	30	1.3
10	ወረባቦ	31	1.2
11	መቅደላ	32	1.2
12	ወረዒሉ	33	1.2
13	ለገሂዳ	34	1.2
14	ተሁለደሬ	35	1.2
15	ደሴ ዙሪያ	36	1.2
16	ተንታ	37	1.2
17	አልብኮ	38	1.2
18	አርጎባ ልዩ ወረዳ	39	1.3
19	ሳይንት አጅባር	40	1.3
20	ደላንታ	41	1.2

ተ.ቁ	ምስራቅ ጎጃም 184	ኮድ	ማስገ
1	አዋበል	42	1.2
2	አነደድ	43	1.2
3	ባሶሊበን	44	1.2
4	ቢቡኝ	45	1.2
5	ደባይጥሳትግን	46	1.2
6	ደጀን	47	1.2
7	ጎንቻ ሲሶ እነሲ	48	1.2
8	ጎዛምን	49	1.2
9	ስናን	50	1.2
10	ሁለት እጁእነሲ	51	1.2
11	እናርጅ እናውጋ	52	1.2
12	እንማይ	53	1.2
13	ማቻክል	54	1.2
14	ሸበል በረንታ	55	1.2
15	ሞጣ ከተማ	56	1.1
16	እንብሲ ሳር ምድር	57	1.2
18	ሰዴ	58	1.2

ቅፅ-001

ተ.ቁ	ደ/ጎንደር 185	ኮድ	ማባዣ
1	ታችጋይንት	59	1.2
2	ደራ	60	1.2
3	አብናት	61	1.2
4	እስቴ	62	1.2
5	አንዳቤት	63	1.2
6	ፎገራ	64	1.2
7	ሊቦ ከምከም	65	1.2
8	ላይጋይንት	66	1.2
9	ወረታ ከተማ	67	የለውም
10	ስማዳ	68	1.2
11	ፋርጣ	69	1.2
12	ለዴ ሙጃ	70	1.2
13	ጉና ቤጌምድር	71	1.2
14	መቀጣዋ	72	1.3

ተ.ቁ	ሰሜን ሸዋ 186	ኮድ	ማባዣ
1	በረኸት	73	1.3
2	ምንጃር ሸንኮር	74	1.2
3	አንጎለላ ጠራ	75	1.2
4	አንኮበር	76	1.2
5	በባሶናወራና	77	1.2
6	ኤፍራታና ግድም	78	1.2
7	መንዝ ጌራ ምድር	79	1.2
8	መንዝቀያ ገብርኤል	80	1.2
9	ሃገረ-ማርያም	81	1.2
10	ሊያደብርና ዋዩ	82	1.2
11	አንሳሮ	83	1.2
12	ቀወት	84	1.3
13	መንዝላሎ ምድር	85	1.2
14	መንዝማማ ምድር	86	1.2
15	መርሃቤቴ	87	1.2
16	ሚዳወርሞ	88	1.3
17	ጣርማበር	89	1.2
18	ሞረትናጅሩ	90	1.2
19	ሸዋሮቢት ከተማ	91	1.1
20	አንጾኪያ ገምዛ	92	1.2
21	ግሼራቤል	93	1.4
22	አሳግርት	94	1.2
23	ቀጮናወደራ	95	1.2

ተ.ቁ	አዊ ብ/አሰ 187	ኮድ	ማባዣ
1	ዳንግላ ዙሪያ	96	1.2
2	ዳንግላ ከተማ	97	የለውም
3	ጃዊ	98	1.5
4	እንከሻ ጓጉሳ	99	1.2
5	ጓንጓ	100	1.2
6	ዚገም	101	1.4
7	ቻግኒ ከተማ	102	1.1
8	ፋግታ ለኮማ	103	1.2
9	ባንጃ	104	1.2
10	ጓጉሳ	105	1.2
11	እንጂባራ ከተማ	106	የለውም
12	አየሁ ጓጉሳ	107	1.2

ተ.ቁ	ማ/ጎንደር 188	ኮድ	ማባዣ
1	ምዕራብ በላሳ	108	1.4
2	አለፋ	109	1.2
3	ጣቁላ	110	1.2
4	ጠገዴ	111	1.5
5	ወገራ	112	1.2
6	ምሰ/በለሳ	113	1.4
7	ታች አርማጭሆ	114	1.5
8	ኪንፋዝ በገላ	115	1.4
9	ምዕራብ ደምቢያ	116	1.2
10	ምስ/ደምቢያ	117	1.2
11	ጎንደር ዙሪያ	118	1.2
12	ላይ አርማጭሆ	119	1.2
13	ነባሩ ጭልጋ	120	1.2
14	ጭልጋ ቁ. 1	121	1.2
15	ማዕ/አርማጭሆ	122	1.5

ቅፅ-001

ተ.ቁ	ዋግ ኽምራ 189	ኮድ	ማባዣ
1	ሰቆጣ ዙሪያ	123	1.2
2	አበርገሌ	124	1.5
3	ዳሀና	125	1.2
4	ጋዝጊብላ	126	1.2
5	ዝቋላ	127	1.5
6	ሰቆጣ ኩተማ	128	1.1
7	ስሀላ ሰየምት	129	1.5
8	ጻግብጂ	130	1.3
9	ኮረም ከ/አሰተዳር	131	1.1
10	አፍላ	132	1.3
11	ዛታ	133	1.3

ተ.ቁ	ምዕራብ ጎጃም 190	ኮድ	ማባዣ
1	ቡሬ ከተማ	134	1.1
2	ቡሬ ዙሪያ	135	1.2
3	ደጋ ዳሞት	136	1.2
4	ደምበጫ	137	1.2
5	ወንበርማ	138	1.2
6	ጃቢ ጠሀናን	139	1.2
7	ሠከላ	140	1.2
8	ቋሪት	141	1.2
9	ፍ/ሠላም	142	የለውም

ተ.ቁ	ምዕራብ ጎንደር 191	ኮድ	ማባዣ
1	ገንዳውሃ	143	1.3
2	አዳኝ አገር ጫቆ	144	1.5
3	ምዕ/ አርማጭሆ	145	1.5
4	መተማ	146	1.5
5	ቋራ	147	1.5

ተ.ቁ	አሮሞ ብ/አስተዳደር 192	ኮድ	ማባዣ
1	አርጡማ ፉርሲ	148	1.2
2	ባቲ ዙሪያ	149	1.3
3	ባቲ ከተማ	150	1.1
4	ደዋ ጨፋ	151	1.2
5	ደዌ ሀረዋ	152	1.3
6	ጅሌፕሙ.ጋ	153	1.3
7	ኬሚሴ ከተማ	154	የለውም

ተ.ቁ	ሰሜን ጎንደር 193	ኮድ	ማባዣ
1	ጠለምት	155	1.5
2	ጃናሞራ	156	1.4
3	በየዳ	157	1.5
4	ደባርቅ ከተማ	158	የለውም
5	ዳባት	159	1.2
6	ደባርቅ ዙሪያ	160	1.2
7	አዲአርቃይ	161	1.5
8	ምስ/ጠለምት	162	1.5
9	ምዕ/ጠለምት	163	1.5
10	ማይጠብሪ ከ/አሰ	164	1.3

ተ.ቁ	ሰሜን ወሎ 194	ኮድ	ማባዣ
1	ቡግና	165	1.3
2	ላስታ	166	1.2
3	ዋድላ	167	1.2
4	ዳውንት	168	1.2
5	ግዳን	169	1.2
6	ላሊበላ ከተማ	170	1.1
7	ቆቦ ከተማ	171	1.1
8	ጉባላፍቶ	172	1.2
9	ሀብሩ	173	1.2
10	ራያ ቆቦ	174	1.2
11	መቄት	175	1.2
12	አንጎት	176	1.2
13	ጋዞ	177	1.2
14	አላማጣ ከተማ	178	1.1
15	ራያ አላማጣ	179	1.2
16	ራያ ባላ	180	1.2

ቅፅ-002

ተ.ቁ	የዞኑ ስም	ለዞኑ የተሰጠ ኮድ	ማብራሪ	
1	ሰሜን ጎጃም	181	የለውም	ይህ ማለት ሰሜን ጎጃም የሞላሁትን ወረዳ ማግኘት ካልቻልኩ ሰሜን ጎጃም ይሁን እንጂ በየትኛውም ወረዳ ልመደብ 181 ማለት ነው።
2	ወ/ጠ/ሰ/ሁ	182	የለውም	ይህ ማለት ወ/ጠ/ሰ/ሁ የሞላሁትን ወረዳ ማግኘት ካልቻልኩ ወ/ጠ/ሰ/ሁ ይሁን እንጂ በየትኛውም ወረዳ ልመደብ 182 ማለት ነው።
3	ደቡብ ወሎ	183	የለውም	ይህ ማለት ደቡብ ወሎ የሞላሁትን ወረዳ ማግኘት ካልቻልኩ ደቡብ ወሎ ይሁን እንጂ በየትኛውም ወረዳ ልመደብ 183 ማለት ነው።
4	ምስራቅ ጎጃም	184	የለውም	ይህ ማለት ምስራቅ ጎጃም የሞላሁትን ወረዳ ማግኘት ካልቻልኩ ምስራቅ ጎጃም ይሁን እንጂ በየትኛውም ወረዳ ልመደብ 184 ማለት ነው።
5	ደቡብ ጎንደር	185	የለውም	ይህ ማለት ደቡብ ጎንደር የሞላሁትን ወረዳ ማግኘት ካልቻልኩ ደቡብ ጎንደር ይሁን እንጂ በየትኛውም ወረዳ ልመደብ 185 ማለት ነው።
6	ሰሜን ሸዋ	186	የለውም	ይህ ማለት ሰሜን ሸዋ የሞላሁትን ወረዳ ማግኘት ካልቻልኩ ሰሜን ሸዋ ይሁን እንጂ በየትኛውም ወረዳ ልመደብ 186 ማለት ነው።
7	አዊ ብ/አስ	187	የለውም	ይህ ማለት አዊ ብ/አስ የሞላሁትን ወረዳ ማግኘት ካልቻልኩ አዊ ብ/አስ/ዞን ይሁን እንጂ በየትኛውም ወረዳ ልመደብ 187 ማለት ነው።
8	ማዕከላዊ ጎንደር	188	የለውም	ይህ ማለት ማዕከላዊ ጎንደር የሞላሁትን ወረዳ ማግኘት ካልቻልኩ ማዕከላዊ ጎንደር ይሁን እንጂ በየትኛውም ወረዳ ልመደብ 188 ማለት ነው።
9	ዋግ ኽምራ	189	የለውም	ይህ ማለት ዋግ ኽምራ ብ/አስ/ዞን የሞላሁትን ወረዳ ማግኘት ካልቻልኩ ዋግ ኽምራ ብ/አስ/ዞን ይሁን እንጂ በየትኛውም ወረዳ ልመደብ 189 ማለት ነው።
10	ምዕራብ ጎጃም	190	የለውም	ይህ ማለት ሰሜን ጎጃም የሞላሁትን ወረዳ ማግኘት ካልቻልኩ ሰሜን ጎጃም ይሁን እንጂ በየትኛውም ወረዳ ልመደብ 190 ማለት ነው።
11	ምዕራብ ጎንደር	191	የለውም	ይህ ማለት ምዕራብ ጎንደር የሞላሁትን ወረዳ ማግኘት ካልቻልኩ ምዕራብ ጎንደር ይሁን እንጂ በየትኛውም ወረዳ ልመደብ 191 ማለት ነው።
12	ኦሮሞ ብ/አስ	192	የለውም	ይህ ማለት ኦሮሞ ብ/አስ/ዞን የሞላሁትን ወረዳ ማግኘት ካልቻልኩ ኦሮሞ ብ/አስ/ዞን ይሁን እንጂ በየትኛውም ወረዳ ልመደብ 192 ማለት ነው።
13	ሰሜን ጎንደር	193	የለውም	ይህ ማለት ሰሜን ጎንደር የሞላሁትን ወረዳ ማግኘት ካልቻልኩ ሰሜን ጎንደር ይሁን እንጂ በየትኛውም ወረዳ ልመደብ 193 ማለት ነው።
14	ሰሜን ወሎ	194	የለውም	ይህ ማለት ሰሜን ወሎ የሞላሁትን ወረዳ ማግኘት ካልቻልኩ ሰሜን ወሎ ይሁን እንጂ በየትኛውም ወረዳ ልመደብ 194 ማለት ነው።